ሚያዝያ 22 ቀን 2005 ዓ.ም

ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርት

አጭር መግለጫ

የተከበሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀፅ 2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 18 እንዲሁም በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተሰጠው ስልጣን መሠረት መ/ቤቱ ኦዲት ያደረገውንና ያስደረጋቸውን የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርት፣ እንዲሁም ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያቀርብ የተደነገገ በመሆኑ፣ በዚሁ መሠረት በ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲትና በተመረጡ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲቶች ዕቅድ ክንውን ሪፖርትና የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ዕቅድ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት፤

1. በልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ላይ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔና አካባቢ ኦዲት እና

በመሠረታዊ አገልገሎት ከለላ ፕሮግራም ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍ (Protection of Basic Services) ተከታታይ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች ናቸው፡፡

2. ሪፖርቱ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በመ/ቤታችን የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት የተደረጉትን በውጭ እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያካትታል፡፡

3. በዚህ ሪፖርት ውስጥ የሚቀርቡ የ2004 በጀት ዓመት የተለያዩ የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሣብ የኦዲት ዕቅድና ክንውን እና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴን ያጠቃለለ ነው፡፡

4. የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች እንዲሁም በ17 የክዋኔ ኦዲት ጥረዞች ለም/ቤቱ የቀረቡ ስለሆነ፣ እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በጥልቀት ተዘጋጅቷል፡፡ የሪፖርቶቹም ቅጅ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

5. እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ እንደተጠናቀቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ በአብዛኛው የመውጫ ውይይት (Exit Conference) ከመደረጉም ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ተልኮላቸው መ/ቤቶቹ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል፡፡

6. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ሲሆኑ፣ ኦዲቱም የተከናወነው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነትና አግባብነት ሙሉ በሙሉ ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የ2004 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሣብ ኦዲት ዕቅድና ክንውን

የፋይናንስና ሕጋዊኒት ኦዲትን በተመለከተ

7. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 63/2 መሠረት የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ሂሳባቸውን በመዝጋት ለኦዲት ማቅረብ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ በሌላም በኩል መ/ቤታችንም በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች ሂሳባቸውን ዘግተው ሲያቀርቡ ኦዲቱን በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ማለትም እስከ ታህሣሥ 30 በማጠናቀቅ ሪፖርቱን ለኦዲት ተደራጊዎች ለመስጠት ግብ ጥሏል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችለው የኦዲት ካላንደርና ዘዴ ላይ ለውጥ በማድረግ ኦዲቱ የሂሳብ መዝጋትን ሳይጠብቅ በየዓመቱ በጥር ወር ተጀምሮ በተከታዩ ዓመት ታህሣሥ ላይ የሚጠናቀቅበት ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉ ይታወሳል፡፡

8. በዚህም መሠረት በ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 129 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን ኦዲት እንደሚደረጉ ታሳቢ የተደረጉትን 8 መ/ቤቶች ጨምሮ በ125 መ/ቤቶች የኦዲት ሥራ በማከናወን የኦዲት ሽፋኑን 96.7% ለማድረስ መታቀዱ ይታወሳል፡፡ በመ/ቤታችን በኩል ኦዲት ለማድረግ ከታቀዱት 117 መ/ቤቶች ውስጥ ሂሳቡን ዘግቶ ለኦዲት ካላቀረበው 1 መ/ቤት በስተቀር የ116 መ/ቤቶችና በጥያቄ የቀረቡ 7 ልዩ ኦዲት የተከናወነ ሲሆን፤ በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን በኩል ኦዲት ለማድረግ የታሰቡት 8 በድምሩ የ124 የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲት በመከናወኑ የፋይናንስና ህጋዊነት የኦዲት ሽፋኑን 96.12% ለማድረስ ተችሏል፡፡

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች

9. የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን በ116 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች እና በ283 የወረዳና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ

ለየመ/ቤቶቹ የላከ ሲሆን፣ ሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባሕርይ አንፃር ከ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መግለጫ	**በፌዴራል መንግሥት ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት**		**የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ተከታታይ ኦዲት**	
	2003	2004	2003	2004
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው	57	49	6	13
ከጥቅት ጉድለቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌት ያለበት አስተያየት	52	48	255	270
አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለጽ አስተያየት የተሰጠባቸው	7	6	1	
የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	13	13	-	
ሂሳባቸውን በወቅቱ ባለመዝጋታቸው አስተያየት ያልተሰጠባቸው	2	1	-	
ድምር	131	117	262	283

<u>በፌዴራል መንግሥት የልዩ ልዩ መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች</u>

10. መ/ቤታችን ምክር ቤቱ ያጸደቀው በጀት የፋይናንስ አስተዳደር ሕጉ፣ ደንብና መመሪያ በሚፈቅድው መሠረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ ባከናወነው ኦዲት በርካታ የሂሳብ አያያዝ ግድፈቶች እና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸው ከደንብና መመሪያ ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች የተገኙ ሲሆን፤ የም/ቤቱን ትኩረት ሊያገኙ

ይገባል ተብሎ የታመነባቸው አንኳር አንኳር ግኝቶች ብቻ ተለይተው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

<u>የጥሬ ገንዘብ ጉድለት</u>

11. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝና አጠባበቅ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ3 መ/ቤቶች ብር 247,210.19 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

12. በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል ልዩነት በ2 መ/ቤቶች ቆጠራው በብር 133,466.99 በማነስ እና በ9 መ/ቤቶች በብር 3,433,156.03 በመብለጥ የታየ ሲሆን በአጠቃላይ በ24 መ/ቤቶችም የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንደሚታዩ በኦዲታችን ወቅት አረጋግጠናል፡፡

13. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳቦች ላይ ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፤ በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በቆጠረ ከተገኘው ጋር ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ፤ በማነስና በመብለጥ የታየው ልዩነትም ተጣርቶ እንዲተካ ወይም ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ እና በ24ቱ መ/ቤቶችም የታዩ የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዲስተካከሉ አሳስበናል፡፡

<u>የውዝፍ ተሰባሳቢ ሂሣብ</u>

14. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 በተደነገገው መሠረት ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱ ሲጣራ በ57 መ/ቤቶች ብር 1,369,377,900.98 በደንቡ መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የትምህርት ሚኒስቴር ብር 401,757,697.18፤ የግብርና ሚኒስቴር 64,602,005.48፤ የግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጣና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ 155,597,701.70፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር 173,756,807.75፤ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር

159,455,023.31፣ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 86,367,964.14፣ በሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና የፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 83,081,758.27፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 69,022,422.95፣ የፌዴራል ፖሊስ 29,778,302.26 እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 21,399,805.70 ይገኙበታል፡፡

15. በተጨማሪም በተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ የሚታዩ ዋና ዋና የአሰራር ችግሮች፣ ዕዳው ከማን እንደሚፈለግ ዝርዝር ማስረጃ ባለመኖሩ ከሰራተኛው የሚፈለገውን ቀሪ እዳ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣ በአንዳንድ መ/ቤቶች ገንዘቡ ወጪ ተደርጎ ለመሰጠቱ ማስረጃው ባለመቅረቡ የተሰብሳቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ያልተለመደ ሚዛን /Abnormal balance/ ማሳየቱ፣ በአንዳንድ መ/ቤቶች የተሰብሳቢ ሂሳብ ሠነዱ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑና ከመቼ ጀምሮ የሚፈልግ ሂሳብ እንደሆነ የሚገልጽ ማስረጃ እና ተቀጽላ ሌጀር ያልተቋቋመ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ ናቸው፡፡

16. ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣቡ በየመ/ቤቶቹ የሥራ ማስኬጃ ላይ ተፅእኖ በማሳደር የሥራ እንቅስቃሴ የሚያዳክምና የበጀት አጠቃቀም ላይ ተጽእኖ ከመፍጠሩም በላይ ለምዝበራና ለብክነት በር የሚከፍት በመሆኑ መ/ቤቶቹ የፋይናንስ ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው እንዲያወራርዱ አሳስበናል፡፡

<u>የገቢ ሂሣብ</u>

17. የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

<u>በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ</u>

18. የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በናሙና በታዩት በ4 መ/ቤቶችና በ6 የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 29,205,484.95 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ

እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ያልተሰበሰበ የገቢ ሂሣብ መኖሩ ታውቋል፡፡

19. በአዋጁ በመሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች መካከል ምስራቅ አዲስ አበባ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤት ብር 25,090,951.15 እና ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 1,066,483.48 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

20. በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

21. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በስሩ ባሉ ስድስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው ብር 853,920,158.83 እና በሌሎች 6 መ/ቤቶች ብር12,250,953.19 በድምሩ ብር 866,171,112.02 ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

22. በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት እንዲሁም ለሀገሪቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሳካት ወሳኝ በመሆኑ፤ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ

23. በበጀት ዓመቱ በተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶች የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ማኒስቴር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ5 መ/ቤቶች የሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ብር24,606,079.30 ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡

24. በሌላ በኩል 15 መ/ቤቶች ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ገቢ የሚሰበስቡ ቢሆንም የገቢ ሪፖርት የማያዘጋጁ በመሆኑ ሂሳቡን ኦዲት ማድረግ

አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም 5 መ/ቤቶች የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሳያስፈቅዱ የገቢ ደረሰኝ አሳትመው ገቢ እንደሚሰበስቡ ታውቋል፡፡

25. ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪም ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ስለሚያደርግ መ/ቤቶች የሚሰበስቡትን ማንኛውም የመንግስት ገቢ ሕጋዊ በሆነ መንገድ በታተሙ ደረሰኞች ብቻ በመጠቀም እንዲሰበስቡና በሂሳብ መግለጫዎቻቸውም በመካተት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

<u>የወጪ ሂሣብ</u>

26. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሠረት በአግባቡ መጠቀማቸውን፣ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡንና ሂሣቡም በትክክል መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

<u>የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ</u>
<u>በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሣብ</u>

27. በወጪ ለተመዘገቡ ሂሣቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ13 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 132,364,911.31 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

28. ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ የተከናወነውን ሥራ በሚያሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ በቀረበው ጥያቄ ብቻ የተፈፀመ ክፍያ፤ በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሣቦች ጎላ ያሉት ናቸው፡፡

29. ማንኛውም ሂሣብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያ መሠረት ማስረጃዎች መሟላታቸው እንዲረጋገጥ፣ ያልተሟሉት ማስረጃዎች እንዲሟሉና ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ

30. በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ22 መ/ቤቶች ብር 13,803,411.08 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

31. በመሆኑም የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ በቂ ማስረጃ እንዲቀርብለት፣ አለበለዚያ ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ አሳስበናል፡፡

የግዢ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዢዎች

32. የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ30 መ/ቤቶች ብር 353,568,759.15 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

33. ከደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር 240,221,573.63፤ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 36,198,641.27፤ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 20,341,230.59፤ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 14,082,063.07 ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 8,755,250.38 ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,745,462.35 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

34. ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ መፈጸም ያለበትን ግዥ ውድድር ሳይደረግ መፈጸም እና በውስን ጨረታው የግዥ ዘዴ በቂ አቅራቢዎች ሳይጋብዙ ግዥን ማከናወን የሚሉት ይገኙበታል፡፡

35. የግዢ መመሪያን ሳይከተሉ ግዢ መፈጸም ለምዝበራና ለጥራት መጓደል የሚያጋልጥ በመሆኑ የመንግሥት ግዢ ደንብና መመሪያን አክብረው በማይሠሩ መ/ቤቶች ላይ የተጠናከረ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

36. ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈጸሙ ሲጣራ በ21 መ/ቤቶች ብር 137,363,575.83 ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

37. በግንባታ ቦታ ላይ ላሉ ዕቃዎች (materials on site)፣ ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመፈጸም፣ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈልና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የኃላፊነት አበል ለዩኒቨርሲቲ የስራ አመራሮች ክፍያ በመሳሰሉት ምክንያቶች በጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር 77,611,944.97፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 34,771,018.34 እና ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,825,188.84 ወጪ ያደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

38. በተጨማሪም የቀድሞው የፌዴራል ሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽን በቁጥር መ30/ጠ/ጠ13137/820 በቀን 5/13/2001 ዓ.ም በተጻፈ ሠርኩላር የትርፍ ስዓት ክፍያ ተግባራዊ እንዳይሆን መመሪያ ያስተላለፈ ቢሆንም፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሣያስፈቅድ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በ2004 በጀት ዓመት ለትርፍ ሰዓት ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

39. በመሆኑም ከደንብና መመሪያ ውጪ ያለአግባብ የተከፈለው ሂሣብ ተመላሽ እንዲሆንና ለወደፊቱም ደንብና መመሪያዎች ተከብረው መሰራት እንዳለበት ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች አሳስበናል፡፡

በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

40. በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ በደንብና በመመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ12 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 546,599,723.27 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

41. ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 302,924,907.46፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር 123,905,491.52፣

ትምህርት ሚኒስቴር ብር 47,988,495.21 እና ማዕድን ሚኒስቴር ብር 28,630,317.74 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

42. መሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፤ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብለት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርተችን አሳስበናል፡፡

__በብልጫ የተከፈለ ወጪ__

43. በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡ በ 7 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግዢዎች ብር 542,220.60 እና ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በ4 መ/ቤቶች ብር 851,589.66 በድምሩ ብር 1,393,810.26 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

44. በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፤ በድጋሚ ወጪ በማድረግ ወይም ከተገበው ውል ውጭ በመክፈልና ከውሎ አበል ተመንና የትርፍ ሰዓት ክፍያ በላይ በመክፈል የሚሉት ይገኙበታል፡፡

45. በመሆኑም መ/ቤቶች የግዢና ፋይናንስ አስተዳደር ስርዓቱን ተከትለው መፈጸም እንደሚገባቸውና በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

__የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት__

46. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛው ንብረት ለመ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች በብር 20,240,407.36 የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሣቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

47. ከዚህም ውስጥ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 18,870,460.03 እና መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,325,755.75 ለተገዛው ዕቃና ንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልቆረጡት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

48. በተጨማሪም በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ከውጪ ሀገር በድምሩ በአሜሪካን ዶላር 832,255.80 ተገዝተው የመጡ የተለያዩ ማሽነሪዎች ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ ተውቋል፣

49. የዚህ ዓይነት አሠራር ለንብረት ብክነት ስለሚያጋልጥ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ ሊደረግና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው ንብረቶች ለየመ/ቤቶቹ አገልግሎት ለመዋላቸው በማስረጃ እንዲረጋገጥ ለመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ

50. በበጀት ዓመቱ መ/ቤቶች የፈጸሙት ክፍያ ትክክለኛነቱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶች በተለያየ ምክንያት ማስረጃ ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ብር 3,507,062,927.60 ተገኝቷል፡፡

51. የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሣብ ውስጥ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 3,169,110,595.13፤ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ብር 187,857,058.5፤ ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 41,288,852.19፤ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 29,790,947.40 እና ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ብር 14,000,000.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

52. ማንኛውም የመንግስት ባለበጀት መ/ቤት የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፡ ደንብና የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያዎችን ተከትሎ ሂሳቡን መያዝና ኦዲት ማስደረግ ስላለበት እነኚህ መ/ቤቶች ለወደፊቱ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የተሟላ ሠነድ በማደረጀት ሂሳባቸውን እንዲያስመረምሩ አሳስበናል፡፡

በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ

53. ከውስጥ ገቢ እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸው ያወጡትን ወጪ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት አካተው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያቀርቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች የብር 159,482,075.35 ወጪ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ተካቶ በሕጉ መሠረት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የውስጥ ገቢ ሂሳባቸውን በገቢ ሂሳብ ሪፖርት የማያካትቱ 15 የከፍተኛ

ትምህርት ተቋማት በገንዘብ መጠን ያልታወቀ ወጪ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የማያካትቱ በመሆኑ ሂሳቡን ኦዲት ማድረግ አልተቻለም፡፡

54. ይህ አሰራር የዘመኑ የፌዴራል መንግስት አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫን የሚያዛባ ከመሆኑም በላይ ሕገ ወጥ በመሆኑ እንዲስተካከል ባለፉት ዓመታት ሪፖርታችን ቢናሳስብም ሊስተካከል አልቻለም፡፡ ስለሆነም ሊሰበሰብ የሚገባው የመንግሥት ገቢ በአግባቡ እንዲሰበሰብ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ለተከበረው ም/ቤት ሪፖርት እንዲያቀርብ ሊደረግ ይገባል፡፡

የተከፋይ ሂሣብ

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

55. በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ29 መ/ቤቶች ብር 491,128,467.58 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

56. በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 173,824,549.10፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 159,330,268.77፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 64,327,615.57፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር 25,010,347.22 እና የግብርናና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማስተባበሪያ ብር 23,125,504.24 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

57. በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰኔ 30/2004 ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ብር 163,504,599.94 የሠራዊቱ አባላት ደመወዝ ባለመውሰዳቸው ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ሂሣብ የተያዘና መጠኑም እያደገ የመጣ ከመሆኑም በላይ ክፍያው ሳይፈጸም ሂሣቡ በወጪ የተመዘገበ ሲሆን ቀሪው ብር 10,319,949.16 ለበርካታ ዓመታት በተከፋይ የተያዘና ለማን እንደሚከፈል የማይታወቅ መሆኑ ታውቋል፡፡ አሠራሩ ከመንግሥት የሂሣብ አሠራር ውጭ በመሆኑ እንደማንኛውም የፌደራል መንግሥት መ/ቤት ያልተከፈለ ደመወዝ በቀጣዩ ወር መጀመሪያ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት ደመወዝ ካልተከፈላቸው አባላት ጥያቄ

ሲቀርብ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እየተጠየቀ እንዲከፈልና ሌሎችም መ/ቤቶችም በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ የፋይናንስ አስተዳደር ሕጉን ተከትለው ለሚመለከተው አካል እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

58. በተጨማሪም በ12 መ/ቤቶች የተለያዩ የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ ችግር ያለባቸው፣ ያለበቂ ማስረጃ በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገቡ፣ ለማን እንደሚከፈል የሚያመለክት ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ ያልተቻለ፣ በተከፋይ ሂሳብ መግለጫ ያልተካተቱ፣ እንዲሁም ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የሚያሳዩ ተከፋይ ሂሳቦች ተገኝተው አስፈላጊው ማስረጃ እንዲቀርብና ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግላቸው ለየመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>የበጀት አጠቃቀም</u>

<u>ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ</u>

59. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት በ27 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሣብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ሥራ ላይ የዋለ ብር 212,476,799.01 ተገኝቷል፡፡

60. ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ብር 40,976,939.3፣ ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ብር 30,910,509.49፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 28,217,838.81፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 22,225,409.00 እና በማይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት ብር 21,636,005.12 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

61. በመሆኑም መ/ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀት በተገቢው መንገድ የበጀት ዝውውር በማድረግ አስፈቅደው ሥራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

የንብረት አስተዳደር

62. መንግሥት ለቋሚና አለቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው የዕቃና ንብረት አስተዳደር በዚህ ዓመትም አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ፣

ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	21 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱ ያላረጋገጡ	18 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	12 መ/ቤቶች
የቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ	20 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	33 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	3 መ/ቤቶች

መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

63. በተጨማሪም በ10 መ/ቤቶች የተለያዩ ከፍተኛ የንብረት አያያዝና አስተዳደር የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች የሚታይባቸውና ቀደም ባሉት የኦዲት ሪፖርታችንም እንዲያስተካክሉ አስተያየት ተሰጥቶባቸው አሁንም ያልተስተካከሉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

64. በመሆኑም የየመሥሪያ ቤቶቹ የንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲመራ፣ በታዩት ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ፣ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል።

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ

65. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ14 መ/ቤቶች	375 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆመ	በ18 መ/ቤቶች	287 ተሽከርካሪዎች
በተለያዩ ድርጅቶች ሥም ሊቢሬ ያላቸው ወደ መ/ቤቱ ስም ያልተቀየረላቸው	በ4 መ/ቤት	15 ተሽከርካሪዎች

መኖራቸው ታውቋል፡፡

66. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ፣ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው በመግለጽ፤ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ፣ ሊብሬ ያልቀረበላቸው አስፈላጊው ማስረጃ ተሟልቶ እንዲወጣላቸው፣ በሌላ መ/ቤት የተያዙት ሊብሬ በባለቤትነት ወደያዘው መ/ቤት ሊብሬው እንዲቀየርላቸው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

መሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች

67. የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተልኮ ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍነው የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርና፣ የውሃና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

68. በዚህም መሠረት ከሁሉም ክልሎች በናሙና በተመረጡ በ270 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ የክልል ሴክተር ቢሮዎች ተከታታይ ኦዲት (Continuous Audit) እና አንድ ፕሮግራም አቀፍ የሆነ የማጠቃለያ (final audit) ኦዲት ለማካሄድ ታቅዶ በ283 (105%) ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ በሆኑ የሴክተር ቢሮዎች እንደዚሁም ፕሮግራም አቀፍ የሆነውን የማጠቃለያ

(final audit) ኦዲት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ደረጃ በማካሄድ የPBS ኦዲቱን በታቀደው መሠረት ለመፈጸም ተችሏል፡፡

የፌዴራል የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት በተመለከተ

69. በገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርቱ የተላከ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት የታዩት ዋና ዋና ግኝቶች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

70. በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በተለያየ ምክንያት በስህተት የተሰበሰበ ቀረጥ ግብር ከፋዩ በስህተት የከፈለ ለመሆኑ ሲታወቅና በኮሚቴ ሲረጋገጥ በስህተት የተከፈለው ቀረጥ በበጀት ተይዞ ለግብር ከፋዩ ተመላሽ የሚደረግለት ሲሆን በ2004 በጀት ዓመት ተሰብስቦ በበጀት ዓመቱ ለቀረጥ ተመላሽ የተደረገው ብር 2,954,828.92 በገቢ ተመላሽ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ሪፖርት ተመዝግቦ ለሚኒስቴሩ መ/ቤቱ መቅረቡና ሚኒስቴር መ/ቤቱም ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ ማድረግ ሲገባው አለማድረጉና በዚህም ምክንያት የተጠቃለለው የገቢ ሪፖርት በዚያው መጠን ሚዛኑ ከፍ (overstated) እንዲል ማድረጉ፤

71. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀፅ 59 መሰረት ሚኒስቴሩ ከመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚደርሰውን የተመረመረና በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የተስተካከለ ሂሳብ መግለጫ ከማእከላዊ ግምጃ ቤት ሂሳብ ጋር በማጠቃለል የፌዴራል መንግስትን ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማዘጋጀቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በናሙና የታዩት ሶስት ሪፖርት አቅራቢ መስሪያ ቤቶች በተሠጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ሂሳብ መግለጫው ሳይስተካከል ሪፖርት ያቀረቡና ያልተስተካከለውም ሂሳብ መግለጫ በተጠቃለለው የፌደራል መንግስት ዓመታዊ ሂሳብ ውስጥ የተካተተ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የክዋኔና አካባቢ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች በተመለከተ

72. መ/ቤታችን የፋይናንስና የሕጋዊነት (regularity) ኦዲቱን ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ በማሳደጉ በሂደት ትኩረቱን በፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ጥራትና በክዋኔ ኦዲት ላይ የማድረግ አቅጣጫን ለመከተል መወሰኑም ይታወቃል፡፡ በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ኘሮግራሞችና ኘሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መወጣታቸውን ለማረጋገጥ የክዋኔ ኦዲት ይከናወናል፡፡

73. በዚሁ መሠረት ከጥር 2004 በፊት ተጀምረው የዝርዝር ኦዲት ስራቸው ወደዚህኛው የኦዲት ዓመት የዞሩ 5 ኦዲቶችን ጨምሮ 27 የክዋኔ ኦዲቶችን በማካሄድ ከጥር 2004 እስከ ታህሣስ 30 ባለው ጊዜ 19 የክዋኔ ኦዲቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 17 ኦዲቶችን (89.5%) አጠናቅቆ ሪፖርት ለማውጣት ተችሏል፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ ክንውን ከዕቅዱ በ 2 ሪፖርት ወይም በ10.5% በማነስ የተፈጸመ ሲሆን ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ለክንውኑ ማነስ አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡

74. ኦዲታቸው የተጠናቀቁት 17ቱ የክዋኔና የአካባቢ ኦዲቶች ላይ የተገኙት ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በመደበኛ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ

75. የመደበኛ ፓስፖርት የሚፈልግ ማንኛውም ዜጋ አስፈላጊውን መረጃ አሟልቶ ሲቀርብ በዋናው መምሪያ በ 3 ቀናት፣ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በ7 ቀናት ውስጥ የጉዞ ሰነድ ተዘጋጅቶ ሊሰጠው ሲገባ በዋናው መምሪያ እና በናሙና በተመረጡት የደሴ፣ የባህር ዳር እና የሃዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እስከ 90 ቀናት ድረስ የሚያስጠብቅ መሆኑ፤

76. በዋና መምሪያውም ሆነ በናሙና በተመረጡት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እያገኙ ስላሉት አገልግሎት አስተያየት ከተጠየቁት 200 ባለጉዳዮች መካከል 189 (94.5%) የሚሆኑት እየተሰጠ ባለው አገልግሎት አለመርካታቸውን የገለፁ መሆኑ፤

77. የፓስፖርት አሰጣጥ ሂደቱ ረዥም መሆን፤ በሌላ በኩል ለደንበኞች በቂ የሆነ እንክብካቤ አለመኖር፤ ከዝናብና ፀሀይ መከለያና የወረፋ መጠበቂያ ቦታ አለመኖር፤ የመፀዳጃ ቤትና ውሃ አለመኖር፤ የቀጠሮ ቀን አለመከበር፤ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ባለጉዳዮችን የሚረዳ የመረጃ ዴስክ አለመኖር ለደንበኞች አለመርካት እንደምክንያት ከተጠቀሱት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ መሆናቸው፣

78. በዋና መምሪያው ሆነ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስለሚሰጡ አገልግሎቶች እና አገልግሎቶቹ የት እንደሚሰጡ የማስተዋወቅ ሥራ ሊሰራ የሚገባ ቢሆንም፣ መጠይቅ ከተደረገላቸው 200 አገልግሎት ፈላጊዎች ውስጥ 120 የሚሆኑት (60%) የፓስፖርት አገልግሎት በሌሎች የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንደሚሰጥ እንደማያውቁ መግለፃቸው፤

<u>በሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ልማት ላይ ለሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ልማቱ የአካባቢንና የህብረተሰቡን ደህንነት በማይጎዳ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን በተመለከተ</u>

79. በማዕድን ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ አካላት የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ እና የተዘረጋው ስርዓት ተግባራዊነት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘረጋ ቢሆንም፤ በናሙና ከተመረጡትና በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማምረት ፈቃድ ከተሰጣቸው 21 ባለፈቃዶች ውስጥ 14ቱ (67%) የተቀመጠውን መስፈርት አሟልተው ፍቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ማስረጃ እንዲቀርብ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ሊቀርብልን አለመቻሉ፤

80. የማዕድን ምርመራ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆየው ለ3 ዓመት ብቻ ሲሆን ከ3 ዓመት በኃላ መቀጠል የሚፈልጉ ካሉ ግን ለተከታታይ 7 ዓመታት በየዓመቱ የስራ ፕሮግራም በማቅረብ የምርመራ ፈቃድን ማሳደስ ያለባቸው ቢሆንም እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ መታደስ ወይም መሰረዝ የነበረባቸው 81 የምርመራ ፈቃዶች ስለመታደሳቸው ወይም እንዲያሳድሱ ማሳሰቢያ ስለመሰጠቱ ወይም ፈቃዳቸው ስለመሰረዙ የሚያሳይ ማስረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ አለመቅረቡ፤

81. የመንግስት ነፃ የአክስዮን ድርሻ በቀድሞው አዋጅ 2% በአዲሱ አዋጅ ደግሞ 5% እንደሚኖረው የተደነገገ ቢሆንም፣ በአዲቱ ወቅት የመንግስት ነፃ አክስዮን

ድርሻ የሚያስገኘውን ጥቅም በተመለከተ በማዕድን ሚኒስቴር ፈቃድ ከተሰጠቸውና በናሙና ከተመረጡት 21 ማዕድን አምራቾች ውስጥ 20 ባለፈቃዶች ክፍያ የማይፈፅሙ መሆኑ፤

82. የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎችና አያያዛቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ መዘጋጀትና መሰራጨት እንዳለበት በማዕድን ፖሊሲ ሰነድ ላይ የተመለከተ ቢሆንም፣ መመሪያው በሚኒስቴር መ/ቤቱ አለመዘጋጀቱ፤

83. የማዕድን ፈቃድ ጠያቂዎች ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሊያቀርቡ፣ የጥናቶች ትክክለኛነት የሚረጋገጥበት ሥርዓትም ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግና የጥናቱ ተግባራዊነት ላይ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ሲገባ፣ የማምረት ፈቃድ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከወሰዱትና በናሙና ከተመረጡት 21 ባለፈቃዶች ውስጥ 16 ባለፈቃዶች (76%) የሚሆኑት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አቅርበው ፈቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ማስረጃ አለመቅረቡ፤

84. የማዕድን ባለፍቃዶች የአካባቢ ተፅዕኖ መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ሊመድቡና ፈንዱ በስራ ላይ የሚውልበትን የአሰራር ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸው ቢሆንም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እና በኦሮሚያ ክልል እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር እና ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ከወሰዱት ባለፈቃዶች ለመልሶ ማቋቋሚያ የሚሆን ፈንድ ፈቃድ ሲሰጣቸው በውሉ ላይ ከሚገለጽ የገንዘብ መጠን በስተቀር የተመደበው ገንዘብ የት መቀመጥ እንዳለበትና ስራ ላይ ስለመዋሉ ክትትል የሚደረግበት ስርዓት አለመኖሩ፤

85. ለመንገዶች ግንባታና ጥገና አገልግሎት በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና በክልል የገጠር መንገድ ባለሥልጣኖች እንዲሁም በእነርሱ በኩል ጨረታ አሸንፈው ኮንትራት የሚወስዱ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በህግ በተደነገገው መሰረት በነፃ የሚጠቀሙ ቢሆንም በማዕድን አዋጁ መሰረት አካባቢን መልሶ ለማቋቋም የሚያገለግል ፈንድ የማይመድቡ እና የመንገድ ግንባታቸውን ጨርሰው ቦታውን ለቀው ከመሄዳቸው በፊት የመልሶ ማቋቋም ስራዎች የማይሰሩ መሆኑ፤

በመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታ ፈንድ አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ

86. አዋጅ ቁጥር 714/2003 ከመውጣቱ በፊት አሰሪ መ/ቤቶች ከሰራተኞቻቸው ደመወዝ እየቆረጡ የሰበሰቡትን የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ማድረጋቸውን ለመከታተል የተዘረጋ ስርአት ያልነበረ ሲሆን፣ አዋጁ ከወጣም በኋላ በተለይ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከሰራተኞቻቸው የሰበሰቡትን የጡረታ መዋጮ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ እንዲችሉ ኤጀንሲው ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር ውል የተዋዋሉ ቢሆንም፣ መሰብሰብ ያለበትን የጡረታ መዋጮ በውሉ መሰረት ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ የሚያስችል ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

87. ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር በተደረገው የውል ስምምነት ላይም ተጠቃሎ ወደ ጡረታ ፈንድ ገቢ የተደረገውን የጡረታ መዋጮ ገቢ ያደረጉትን እያንዳንዱን የመንግሥት የልማት ድርጅት እና ሰራተኞች ለማወቅ እንዲቻል ዝርዝር መግለጫ በማዘጋጀት ከባንክ ዴቢት አድቫይስ ጋር ገንዘቡ ለጡረታ ፈንዱ በተላለፈበት ወር እስከ ቀጣዩ ወር 30ኛው ቀን ድረስ ለኤጀንሲው መላክ እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም ባለስልጣኑ በውሉ መሰረት እንዲፈጽም ባለመደረጉ አሰሪ መ/ቤቶች ያስገቡለትን ብቻ ለኤጀንሲው በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ከማድረጉ ውጪ ከየትኛው መ/ቤት፣ ዞን፣ ወረዳ እንደተሰበሰበ ባለመታወቁ የተነሳ የትኛው መ/ቤት የጡረታ መዋጮውን በወቅቱ ገቢ ማድረጉንና አለማድረጉን ለመለየት አለመቻሉ፤

88. በፌዴራልም ሆነ በክልል የጡረታ መዋጮ ከፋይ ከሆኑ አሰሪ መ/ቤቶች መሰብሰብ የሚገባው ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ስለመሰብሰቡ ኤጀንሲው ምርመራ በማድረግ እርምጃ መውሰድ ያለበት ቢሆንም መሰብሰብ የሚገባው ውዝፍ የጡረታ መዋጮ መኖሩን እንጂ መጠኑ ምን ያህል እንደሆነና ውዝፍ መዋጮ ያለባቸው መ/ቤቶች የትኞቹ እንደሆኑ ተለይተው የማይታወቁ መሆኑ፤

89. የሚፈለግባቸውን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ገቢ ያላደረጉ የክልል መንግሥታት በአዋጅ ቁጥር 714/2003 መሰረት የፌዴራል መንግሥት ከሚሰጣቸው የድጎማ በጀት ላይ ተቀንሶ ለኤጀንሲው ገቢ መደረግ ሲገባ፣ ኤጀንሲው በእያንዳንዱ

የመንግሥት መ/ቤት ላይ ክትትል አድርጎ አለመሰብሰቡን፣ እንደዚሁም ከመጋቢት 14 እስከ ግንቦት 30 2004 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ በቀረበው የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት በድምሩ ብር 118,114,069.00 በአሰሪ መ/ቤቶች ላይ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ መኖሩ ተረጋግጦ መተማመኛ የተሰጠ ቢሆንም ገንዘቡ ገቢ ስለመደረጉ ማስረጃ ሊቀርብ አለመቻሉ፤

90. በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 መሰረት የበጀት አመቱ ባለቀ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ የኤጀንሲውን ሂሳቡን ኦዲት ማስደረግ ሲገባ የ2003 እና 2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ባለመዘጋቱ የጡረታ ፈንዱ ሂሳብ ከ2002 በኋላ ኦዲት ያልተደረገ መሆኑ፤

<u>የቀረጥ ነጻ ንግድ አሠራርና አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

91. በቀረጥ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላት፣ ሥራው ላይ ከመሰማራታቸው በፊት የቀረጥ ነጻ ንግድ ሥራ ፈቃድ ማውጣትና በወቅቱ ማደስ የሚኖርባቸው ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት፣ በቀረጥ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው በመስራት ላይ የሚገኙት የግል የቀረጥ ነጻ ድርጅቶች በቀረጥ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል የህግ መሰረት እና የቀረጥ ነጻ ንግድ ሥራ ፈቃድ የሌላቸው መሆኑ፤

92. በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 እና በተሻሻለውም አዋጅ ቁጥር 686/2002 መሠረት የቀረጥ ነጻ ንግድ ዘርፍ የቀድሞው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መ/ቤት የንግድ ሥራ ፈቃድ ከሚሰጥባቸው የንግድ ሥራ ዘርፎች ዝርዝር ውስጥ ካለመካተቱም በላይ በቀረጥ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላት ማሟላት የሚገባቸው መስፈርትም አለመዘጋጀቱ፤

93. በቀረጥ ነፃ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ገንዘብ በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ ማውጣትና በየወቅቱ ማሳደስ ያለባቸው ቢሆንም በቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩት አንድ የግል ድርጅት በአዲስ አበባ ኤርፖርት ተርሚናል አንድ እና ሁለት ውስጥ ላሉት ሁለት ሱቆቹ በውጭ ምንዛሪ ለመገበያየት የሚያስችል ፈቃድ ሳይኖረው፤ በፈቃድ ሰጪና ተቆጣጣሪ አካላትም (የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ

ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች) ፈቃድ ያለው ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ሳይደረግ ከ10 ዓመታት በላይ እየሰረ የሚገኙ መሆኑ፤

94. በሁለቱም ተርሚናል ውስጥ በሚገኙ የወጪ መንገደኞች አዳራሾች ሁለት አይነት የንግድ አሰራር መኖሩ ማለትም ከቀረጥ ነጻ እና ቀረጥ ተከፍሎባቸው የሚሸጡ ዕቃዎች ንግድ የሚካሄድ መሆኑ ህገ-ወጥ ግብይት እንዲካሄድ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር በባለድርሻ አካላት (የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን) ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችል ተገቢው የግብይት ስርዓት እንዲዘረጋ ጥናት ቢያደርጉም ተገቢው የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት በተቀናጀ ሁኔታ ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

95. በኤርፖርት ውስጥ በግለሰቦች የውጭ ሀገር ገንዘቦች ግዢ እና ሽያጭ እንደሚፈጸም በተለያየ ጊዜ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተደረጉ ጥናቶች የተመለከተ ሲሆን ይህንኑ ለማረጋገጥ በኦዲቱ ወቅት ከመስሪያ ቤታችን ለስራው ወጪ ባደረግነው ገንዘብ አንድ የአሜሪካን ዶላር በ23 የኢትዮጵያ ብር የሚመነዘር መሆኑን ለማረጋገጥ መቻሉ፤

96. የጉምሩክ መጋዘን የስራ ፈቃድ አሰጣጥን ለመወሰን በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 24/1990 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሰረት የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ በየበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ከሐምሌ 1 እስከ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም ሊታደስ እንደሚገባ፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ፈቃዱን ያላሳደሰ ድርጅት ደግሞ ከነሐሴ 1 እስከ ነሐሴ 30 ባለው ጊዜ የማሳደሻውን ክፍያ 100% ቅጣት በመክፈል ማሳደስ እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም፣ ሦስቱም የግል ድርጅቶች ከነሐሴ 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃዳቸውን አለማሳደሳቸው፤

97. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 ላይ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ማውጫ እና ማሳደሻ ክፍያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ እንደሚወሰን የተገለጸ ቢሆንም ደንቡ አለመውጣቱ፤

98. ከቀረጥ ነፃ ዕቃዎች ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ ከመግባታቸው በፊት የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ (ዓይነትና ብዛት) በጉምሩክ ተጠናቅሮ የማይያዝ መሆኑ፤

99. በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶች ከቀረጥ ነፃ የሚያስገቧቸውን ጊዜ ያለፈባቸው፤ በጉዞ ወቅት መጠነኛ ጉዳት የደረሰባቸው እና ረዥም አመታትን ያስቆጠሩ ዕቃዎች አወጋገድን በተመለከተ የአፈፃፀም መመሪያ እና ለማስወገድ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ሳይወገዱ ረዥም ጊዜ በሱቅ (በመጋዘን) ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤

በመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የሚታዩ የሥነ-ምግባር ችግሮች እንዲሁም የሚገጥሟቸው ተቋማዊ እና አካባቢያዊ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን በተመለከተ

100. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሚገኙ መምህራንና ተማሪዎች የሥነ-ምግባር ደንብና የዲሲፕሊን መመሪያ ሊዘጋጅ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥበት እና ስለተግባራዊነቱም ክትትል ሊደረግበት ሲገባ በናሙና በታዩት በዲላ፣ በሀዋሳ፣ በጎንደርና በባህር-ዳር ዩኒቨርስቲዎች የመምህራን የሥነ-ምግባር ደንብ ያልተዘጋጀ ሲሆን የተማሪዎች የሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያ ቢኖርም የግንዛቤ ማስጨበጫውን ያላገኙ ተማሪዎች በመኖራቸው መመሪያው በትክክል እየተተገበረ አለመሆኑ፤

101. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የዲላ፣ የሐዋሳ፣ የጎንደርና የባህር-ዳር ዩኒቨርስቲዎች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት ሰዓት አርፍደው ክፍል የሚገቡና የሚቀሩ፣ ፈተና ላይ አይመጣም በማለት ከተማሪው ጋር ተስማምተው የሴሚስተሩን ኮርስ ሳያጠናቅቁ ፈተና የሚሰጡ፣ በወቅቱ በስራ ገበታቸው ላይ ሳይገኙ ቀርተው የፈተና ወቅት ሲደርስ በአጭር ጊዜ ኮርሱን አጠናቀው ፈተና የሚሰጡ፣ የተማሪውን የፈተና ውጤት በወቅቱ የማያሳውቁ፣ ተማሪው በትምህርት ገበታው ላይ መገኘቱን የማያረጋግጡ (Class Atendance የማይዙ) መምህራን መኖራቸውን፤

102. የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎችን ለአጸያፊ ተግባር አሳልፈው የሚሰጡ ደላሎች (ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች አካላት) እንዲጋለጡና በደላሎቹም ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ የማይደረግ በመሆኑ በናሙና በታዩት በአራቱም ዩኒቨርስቲዎች ካምፓሶች ሴት ተማሪዎችን ለአጸያፊ ተግባር አሳልፈው

የሚሰጡ ደላሎች (ተማሪዎች፣ የግቢው ማህበረሰብና የውጭ አካላት) መኖራቸው፤

103. ዩኒቨርስቲዎች በአካባቢያቸው የጫት፣ የሺሻ፣ የመጠጥ፣ የጭፈራ እና የመሳሰሉት ቤቶች እንዳይኖሩ ለማድረግ ከከተማ መስተዳድሮች፣ ከፖሊስ፣ ከማዘጋጃ ቤቶችና ክፍለ ከተሞች ጋር በቅንጅት የሚሰራበት መድረክ ባለመፈጠሩ በዲላ ዩኒቨርሲቲ በአዲሱ ካምፓስ በሀዋሳ ዩንቨርሲቲ ዋናውና የጤና ሳይንስ ካምፓስ፣ በጎንደር ቴዎድሮስና ማራኪ ካምፓስ በባህር-ዳር በዋናው ካምፓስ አካባቢ የጫት፣ የሺሻ፣ እና የመጠዋ ቤቶች እንዲሁም በባህር-ዳር በዘንዘልማና በሀዋሳ በዋናው ካምፓሶች አካባቢ የጫት እርሻዎች መኖራቸው፤

<u>የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት አፈፃፀምን በተመለከተ የተካሄደ ክዋኔ ኦዲት</u>

104. የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ኘሮጀክት ከ1990 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም ውስጥ የቆላ ዝንብን ከ 25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ ነፃ ለማድረግ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ከ13 ዓመታት በኋላ የተከናወነው 6,000 ካ.ኪ.ሜ (24%) ብቻ መሆኑ፤

105. ከብቶችን ስርዓት ባለው መልኩ ኬሚካል ለመቀባት የሚያስችል በቂ በረት ባለመዘጋጀቱ እና ያሉትም በረቶች በአካባቢው ካሉት የከብቶች ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆናቸው አብዛኛው የመቀባቱ ስራ ከበረት ውጪ በማሯሯጥ የሚካሄድ በመሆኑ፣ የኬሚካል ብክነትን እያስከተለ መሆኑ፤

106. በ2002 ዓ.ም እና በ2003 ዓ.ም እንስሳት በማይገቡበት አካባቢ መሬት ለመሬትና በአውሮኘላን የኬሚካል እርጭት ለማከናወን በዕቅድ ቢያዝም፤ እስከ የካቲት 2004 ዓ.ም ድረስ ስራው አለመከናወኑ፤

107. የቆላ ዝንቦች ማምከኛ እና ደምን ከባክቴሪያ ለማፅዳት የሚያገለግል የጨረር (Industrial radiateor Gama ray) መሳሪያ ግዢ የተፈፀመ ቢሆንም ለኢንዱስትሪያል ራዲያተር የሚያስፈልገው ክፍል ግንባታ ስራ ባለመሰራቱ ዕቃው ያለ አገልግሎት መቀመጡ፤

108. ለዕርባታ ማዕከሉና ለመስክ ስራ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣ መድኃኒቶች እና ኬሚካሎች (በፕሮጀክት ማዕከሉ ለዝንቦች እርባታ ክፍል እና ለላቦራቶሪ እንዲሁም ለጨረር ስራ የሚያገለግል) ግዢ በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት አለመከናወኑ፤

109. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ስራውን በደቡብ ክልል ሲጀምር ከክልሉ የግብርና ቢሮ ጋር በቅንጅት መስራት የሚያስችለውን የስምምነት ሰነድ ተፈራርሞ ከቀድሞው የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ኮሚሽንም ይሁንታን ቢያገኝም ከክልሉ ግብርና ቢሮም ሆነ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር መረጃዎችን የማይለዋወጥ መሆኑን፤

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም፣ ክትትል እና ቁጥጥርን በተመለከተ ላይ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት

110. የመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም የተሽከርካሪ ጥገናና አያያዝን ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት እስከ 2004 በጀት ዓመት መጨረሻ አለማውጣቱ፤

111. በናሙና ተመርጠው ከታዩት 11 መ/ቤቶች በ10ሩ የተሽከርካሪዎች ጥገና እና የእንክብካቤ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፤

112. በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች የየሥራ ክፍሎችን የተሽከርካሪ ፍላጎት በማገናዘብ እንደ አስፈላጊነቱ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙ ሠራተኞችን በማቀናጀት ነዳጅን በቁጠባ ለመጠቀም የሚያስችል አሠራር መተግበሩን ለማረጋገጥ በናሙና ተመርጠው ከታዩ 11 መ/ቤቶች 8ቱ አሠራሩ ስለመኖሩ ማስረጃ ለማቅረብ አለመቻላቸው፤

113. ለመንግስት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ ዕደላ ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ የሚወሰን መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ከታዩት 11 መ/ቤቶች በ8ቱ ማስረጃ ሊቀርብ አለመቻሉ፤

114. እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነት፣ በሞዴልና በዕድሜ ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ ምን ያህል ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል ሊታወቅ እና በዚሁ መሠረት ተግባራዊ መደረግ ሲገባው በናሙና ተመርጠው ኦዲት ከተደረጉ 11 መ/ቤቶች በ7ቱ፣ መረጃው ተጠናቅሮ አለመያዙ እና ተግባራዊ አለመደረጉ፤

115. በናሙና በታዩት በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ 6፣ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ 2፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 2፣ በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት 17፣ በግብርና ሚኒስቴር 17 እና በማዕድን ሚኒስቴር 7 በድምሩ 54 ጌጃቸው የማይሰራ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ መሆኑ፤

116. በመንግሥትና ህዝባዊ ድርጅት ተሽከርካሪዎች ግዥ ሥምሪት አጠቃቀምና ጥገና መመሪያ መሰረት በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት የአሰራር ሥርዓት በናሙና ተመርጠው ከታዩት 11 መ/ቤቶች በ8ቱ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

<u>በጋራ ልማት እና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች ውጤታማነት</u>

117. የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ወደ ግል ከተዛወሩ በኋላ በስራ እቅዱ (Business Plan) መሠረት ባለሀብቶች ሥራዎችን እየሰሩ ስለመሆኑ ወጥ የሆነ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ሲገባ ድርጅቶችን የሚያስተዳድሩ ባለሀብቶች በገቡት ውል እና በስራ ዕቅዱ መሰረት እየሰሩ ስለመሆኑ በቂ ክትትል አለመደረጉ፤

118. በጋራ ልማት ኢንቨስትመንትና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሂሳብ ሪፖርቶች የትርፍና ኪሳራ ሪፖርት (Income statemenet) እና የሀብት እና እዳ መግለጫ (Balance sheet) ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ሊቀርብና ፈቃድ ባለው የኦዲት ተቋም ኦዲት መደረግ ሲገባው፣ BM (ቢኤም) ኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት የተያዘው በ2002 ዓ/ም ቢሆንም የሂሳብ መግለጫዎች ለኤጀንሲው አለመለኩና በገለልተኛ ኦዲተሮች ኦዲት አለመደረጉ፤

119. ኤጀንሲው በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨሰትመንት ከግል ባለሀብቱ ጋር በሚያስተዳድራቸው ድርጅቶች የኃላፊነትና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሁም ውል ቢቋረጥ አፈጻጸሙ በስምምነት ሰነዱ መሰረት ሊሆን ሲገባ፣ በውሉ መሠረት ለመንግስት መከፈል የሚኖርበት ብር 106,481,211.57 እና USD 760,000 ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ታህሣሥ 2005 ለመንግሥት ያልገባ መሆኑ፤ (ለዝርዝሩ አባሪ አንድን ይመልከቱ)

የመንግስት ትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ ብድር አሰጣጥ፣ አጠቃቀም እና አሰባሰብን በተመለከተ

120. ኤጀንሲው ከ2003-2007 ባዘጋጀው እስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ለምን ያህል አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች እንደሚሰጥ እና ምን ያህል የብድር ተመላሽ እንደሚሰበሰብ የልማት ድርጅቶችንና አክሲዮን ማህበራትን የፍላጎት ጥናት መሰረት በማድረግ በስትራቴጂክ እቅዱ ውስጥ አለማካተቱና በየአመቱ ተግባራዊ መደረጉን የማያረጋግጥ መሆኑን፤

121. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችና አክስዮን ማህበራት በየበጀት አመቱ መክፈል ያለባቸውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ ገቢ እንዲያደርጉ ደብዳቤ የሚጽፍ እና መርሃ ግብር/የጊዜ ሰሌዳ/ አዘጋጅቶ የሚልክ ቢሆንም 28 የመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክስዮን ማህበራት ፈሰስ ማድረግ የሚገባቸውን ብር 786,952,679 ገቢ ሳያድርጉ በአማካይ ከ2-3 አመታት ያዘገዩ መሆኑን፤

122. ኤጀንሲው በተለያየ ጊዜያት በመንግስት ይዞታ ስር ላሉ አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር በሚሰጥ ጊዜ ውል የሚያስገባ ቢሆንም በገቡት ውል መሰረት የሸቀጦች ጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት ብር 50 ሚሊዮን፣ የከምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ብር 35,369,185፣ የአበቦ እርሻ ልማት ብር 16,316,057፣ ሐማሬሳ የምግብ ዘይት አክሲዮን ማህበር ብር 13,039,877፣ ባቱ ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር ብር 12,440,000፣ ኮስቲክ ሶዳ አክሲዮን ማህበር ብር 3,666,666፣ አዳሚ ቱሉፀረ ተባይ አክሲዮን ማህበር ብር 3,031,625. እንዲሁም ሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ብር 884,000 በድምሩ ብር 134,747,410 ተመላሽ ሳያደርጉ ከ 2 እስከ 6 ዓመት ያዘገዩ እና ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ብድሩን ያልመለሱ መሆኑ፤

123. ኤጀንሲው በመንግስት ይዞታ ስር የነበሩ አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ወደ ግል በሚዛወሩበት ጊዜ በውጭ ኦዲተር ሂሳቡን አስመርምሮ ያለባቸውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ እንዲከፍሉ ውል የሚያስገባ ቢሆንም ከሐረር ቢራ አክሲዮን ማህበር ብር 8,362,019፣ ከአምቦ ማዕድን ውሃ ብር

7,806,125፣ ከቦሌ ቡልቡላ ኮንስትራክሽን ብር 2,381,490 በድምሩ ብር 18,549,634 ገቢ ያልተደረገ የመንግስት ትርፍ ድርሻ ሂሳብ መኖሩ፤

124. ኤጀንሲው በመንግስት ይዞታ ስር የነበሩ አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ወደ ግል በሚዛወሩበት ጊዜ ያለባቸውን የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ገዢ ባለሀብቶቹ እንዲከፍሉ ውል ያስገባ ቢሆንም አርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ብር 10,191,787፣ የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት ብር 11,976,098፣ ታቦር ሴራሚክ ውጤቶች አክሲዮን ማህበር ብር 6,220,831፣ የኢትዮጵያ ቆዳ አክሲዮን ማህበር ብር 11,780,500፣ የሃዋሳ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ብር 4,084,825 በድምሩ ብር 44,254,041 ገዢ ባለሀብቶች በገቡት ውል መሰረት ያልከፈሉት የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር መኖሩ፤

125. ከዚህም ሌላ በኢትዮጵያ መንግስትና ሳይገን ግሩፕ በተባለ የቱርክ ባለሀብቶች ሳይገን ዲማ ጨርቃ-ጨርቅ አክሲዮን ማህበርን ለመመስረት በ2003 ዓ.ም ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የመንግስት ድርሻ ሂሳብ በሚከፈልበት ጊዜ USD 327,107.8 በብልጫ የተከፈለና ያልተመለሰ መሆኑ፤

<u>በግብርና ሚኒስቴር የደን ሀብት ልማት እና ጥበቃ በተመለከተ</u>

126. የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ፖሊሲ፤ ስራቴጂና አዋጅ በ1999 ዓ.ም የወጣ ቢሆንም ይህን ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ተዘጋጅቶ እና ፀድቆ ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ፤

127. በናሙና ተመርጠው የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው ቅድሚያ የተሰጣቸው የሀገሪቱ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች አብዛኞዎቹ የአስተዳደር ፕላን (Site Mamagement Plan) ያልተሠራላቸው፣ የአስተዳደር ፕላን የተሠራላቸው ጥቂት ቢኖሩም የቆየ እና ወቅታዊ አለመደረጉ፣ እንደዚሁም ዳር ድንበራቸው ተከልሎና ተመዝግቦ በሕግ መሠረት ዕውቅና እንዲያገኙ አለመደረጉ፤

128. የሀገሪቱን የደን ሀብት ሁኔታ የሚያሳዩ ወቅታዊ መረጃዎች በየጊዜው እየተጠናቀሩ የማይያዙ ሲሆን ያሉት መረጃዎችም ከ20 ዓመታት በላይ የቆዩ እና እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ መሆኑ፤

129. በሀገር አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ ችግኞች የሚተከሉ ቢሆንም የተተከሉበት አካባቢ፣ የቦታው ስፋት፣ ምን ያህልና ምን አይነት ችግኞች እንደተተከሉ፣

የፀደቀው መጠን፣ የታለመለትን አገልግሎት እስኪሰጥ ድረስ እየተደረገ ያለውን ክትትል የሚያሳይ መረጃ ተጠናቅሮ የማይቀመጥ መሆኑ፤

የፌዴራል መንግስት ቢሮዎች ሕንጻ ግንባታ

130. የመንግሥት የቢሮ ሕንፃዎችን የሚያሠራው የፕሮጀክት ጽ/ቤት በመንግስት የግዥ መመሪያ አንቀፅ 16 መሰረት ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ የጨረታውን አሸናፊ መግለጽና ውል መፈራረም የሚጠበቅበት ሲሆን ለማእከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ፣ ለፕሬስ ድርጅት እና ለገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ተጨማሪ ብሎክ ለማሰራት በግንቦት 2002 ጨረታ ካወጣ በኋላ ኮንትራት ለመፈራረም 9 ወራት መውሰዱ፤

131. በኦዲቱ ወቅት ከታዩ አምስት በግንባታ ላይ ካሉ ፕሮጀክቶች ውስጥ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ተጨማሪ ብሎክ ህንፃ ግንባታ በጥቅምት 2001 ተጀምሮ ሐምሌ 2001 እንደሚጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም እስከ ሰኔ 2004 ድረስ አለመጠናቀቁ፤ እንደዚሁም የፍትህ ሚኒስቴር የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት በሐምሌ 2001 እንዲጠናቀቅ ታስቦ ህዳር 2001 ላይ የተጀመረ ቢሆንም እስከ ሰኔ 2004 ድረስ የተከናወነው 58% ብቻ መሆኑ፤

132. የመንግስት ቢሮዎች ሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እያከናወናቸው ያሉ እና የተጠናቀቁ የቢሮ ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከተያዘላቸው ጊዜ በላይ እስከ ሁለት ዓመት ተጫማሪ ጊዜ መውሰዳቸው፤ በዚህም ምክንያት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የቢሮ ሕንፃ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከተያዘላቸው በጀት በላይ ብር 8.7 ሚሊዮን ያስወጡ መሆኑ፤

133. በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በኮንትራክተሮች መካከል በተፈረመው የኮንትራክት ስምምነት መሰረት የግንባታ እቃዎች የሚቀርቡት በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በኩል ቢሆንም የተያዘላቸውን የጊዜ ሠሌዳ ጠብቀው በወቅቱ ባለመቅረባቸው ግንባታዎቹ በተደጋጋሚ ለወራት የሚቆሙ መሆኑ፤

ቀጥተኛ ክትትል የሚደረግባቸው የግብርና ምርቶች ውጭ ንግድ ማስፋፊያ ሥርዓት አፈጻጸም እና ውጤታማነት በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

134. ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች በተለይ ደግሞ ወደ ዘመናዊ ግብይት ያልገቡት ምርቶች ላይ ተገቢውን የጥራት ደረጃ እንዲያሟሉ በየደረጃው በሚገኙ አካላት በየምርቶቹ ባህሪና ዓይነት ከማሳ እስከ ማዕከል ባለው ሰንሰለት ቼክሊስት በማዘጋጀት የሚደረግ የተጠናከረ ወቅታዊ የጥራት ክትትል አለመኖሩ፤

135. የንግድ ሚኒስቴር ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን ጥራት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ የጥራትና ደረጃ ማዕከላት ምርቶቹ በሚመረቱባቸው አካባቢዎች እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ በማድረግ የማዕከላቱን ውጤታማነት መከታተል ሲኖርበት የጥራትና ደረጃ ማዕከላት የግብርና ምርቶቹ በሚመረቱበት በቅርብ አካባቢ እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ አለማድረጉ፤

136. የንግድ ሚኒስቴር ወደ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት ያልገቡና በውጭ ሀገራት ገበያዎች የሚፈለጉ የግብርና ምርት አይነቶችን እና በየሀገራቱ የሚፈለገውን የጥራት ዓይነት እና መጠን በማጥናት መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተንና በማጠናከር ምርቶቹ ሊመረቱባቸው በሚችሉ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች የግብርናና የግብይት ቢሮዎች እንዲሁም ለላኪዎች እንዲደርሳቸው አለመደረጉ፤

137. የንግድ ሚኒስቴር በክልል ከተደራጁ የኤክስፖርት ልማት ድጋፍ ኮሚቴዎች ጋር በመሆን በሥራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በወቅቱ እንዲፈቱ ለማድረግ የሚያስችል ወቅታዊ የውይይት መድረክ አለመዘጋጀቱ፤

በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ

138. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በስራ ላይ የሚውል የተጠናከረ አገር አቀፍ የህሙማን አላላክና አቀባበል /ሪፈራል/ ስርዓት በመዘርጋት በአገሪቷ ያሉ ሆስፒታሎች ተቀናጅተውና ተናበው እንዲሰሩ ወጥ የሆነ የሪፈራል መመሪያ በማዘጋጀት በመመሪያው ላይ ግንዛቤ እንዲሁም

ታካሚዎችን መሰረት ያደረገ የህክምና ሥነ- ምግባር መመሪያ (ethical and medico-legal regulation) ሊያወጣ ባለመቻሉ የሪፈራል ሆስፒታሎች የእርስ በርስ ትስስር እና በሆስፒታሎች ውስጥ እና በሆስፒታሎች መካከል ተናቦ የመስራት (inter and intra hospital communication) ሁኔታ አለመኖሩ፤

139. በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት ታካሚዎች ሆስፒታል በደረሱ በ2 ስዓት ጊዜ ውስጥ አገልግሎት ሊያገኙ እንዲሁም የሆስፒታሉ ሀኪሞች ለሚያደርጉት የጠዋት ስብሰባ የመሰብሰቢያ ስዓት የጊዜ ገደብ ሊያስቀምጡ ሲገባ የጥቁር አንበሣ ሆስፒታል እና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ ታካሚዎችን የሚቀበሉት ጠዋት ብቻ መሆኑን፤

140. የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አገልግሎት አሰጣጥን በበላይነት የሚመራና የሚከታተል የተጠናከረ የሆስፒታል አስተዳደር ቦርድ ሊያቋቁሙ ሲገባ በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የሆስፒታል አስተዳደር ቦርድ ያልተቋቋመ መሆኑ፤

141. የትምህርት ሚኒስቴር እና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በስራቸው የሚገኙ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚሰጡትን የህክምና አገልግሎት በተቀላጠፈ መልኩ መስጠታቸውን እንዲሁም አስፈላጊ መድሃኒቶችን እና የህክምና መሳሪያዎችን አቅርቦትና አጠቃቀም መኖሩን በቅንጅት ሊከታተሉ ሲገባ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ በመደበኛነት የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ደግሞ አልፎ አልፎ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ክትትልና ድጋፍ የሚያገኙ ሲሆን የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ግን ከትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክ ድጋፍም ሆነ ክትትል የማያገኝ ሲሆን፣ የጎንደርና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ ከትምህርት ሚኒስቴር መደበኛ ክትትል አለማግኘታቸው፤

142. የተመላላሽ ህክምና ክፍል ሐኪሞች በመደበኛ የሥራ ሰዓት ከሥራቸው የማይገኙበት፣ ዘግይተው የሚገቡበት እና የመውጫ ሰዓት ሳይደርስ ቀድመው የሚወጡባቸው ሁኔታዎች በመኖሩ ታካሚዎች (በተለይ ከገጠርና ከሩቅ ቦታ በሚመጡ ታካሚዎች) የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ብዙ ስዓት በመጠበቅ እንደሚጉላሉና ለተጨማሪ ወጪ የሚዳረጉ መሆኑ፤

143. በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ውጤት መሰረት ሁሉም ተመላላሽ ታካሚዎች ስፔሻሊስት፣ ሪዚደንት ሀኪም፣ ጠቅላላ ሀኪም እና ተማሪ ሀኪምን ባካተተ ቡድን እንደሚመረመሩ ቢገልፅም ስፔሻሊስት ሃኪሞች እንደማይገኙ እና ሌሎቹም ቢሆኑ በተሟላ ሁኔታ የማይገኙ መሆኑ፤

144. የጅማና የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች ተመላላሽ ታካሚዎችን ካለ መላኪያ/ሪፈራል ወረቀት ስለሚቀበሉ እና የስፔሻሊስት ሀኪሞች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ህሙማኑ በተማሪ ሀኪም እንዲታዩ የሚደረግ መሆኑ፤

145. የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ እንደ ሦስተኛ ደረጃ ሆስፒታል በቂ የህክምና እና የምርመራ መሣሪያዎች የሌሉት መሆኑ፤

<u>የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት</u>

146. ኢንስቲትዮቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚያስገነባቸው ህንፃዎች በጥናት ላይ የተመሠረቱ እና በታቀደው ጊዜ ሳይዘገዩ ቁጠባና ጥራትን መሠረት ባደረገ መልኩ ሊከናወኑ እና ይህንንም ለማሳካት የሚያስችል ብቃት ያለው የክትትል እና የቁጥጥር ስራ የሚያካሂድ አማካሪ ድርጅት ሊመደብለት እና በግንባታ ሂደትም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ወቅታዊ መፍትሔ በመስጠት ኢንስቲትዩቱ ለህንፃ ግንባታው ላወጣው ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም /value for money/ ማግኘት ሲኖርበት በመጀመሪያው ምዕራፍ የሎት አንድ የህንጻ ግንባታን ለማካሄድ ግሬስ ኢንጅነሪንግ ከተባለ ኮንትራክተር ጋር ባደረገው ስምምነት ስራው ውል በተገባ በአራት መቶ ሰማንያ የካላንደር ቀን ተጠናቆ ለመረከብ ቢዋዋልም ስራው ይጠናቀቃል ከተባለበት ቀን በላይ ስምንት መቶ ዘጠና ሰባት ቀናት ዘግይቶ ጊዜያዊ ርክክብ የተፈጸመ መሆኑ፤

147. ኢንስቲትዩቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት የሚያስፈልጉት በቢዝነስ ኘላኑ ላይ የተገለፁት የምዕራፍ ሁለት እና ሶስት የህንፃ ግንባታዎች በዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ ሊሆኑ ሲገባ በምዕራፍ ሁለት እና ሦስት የሚካተቱት የኢንስቲትዩቱ ወርክሾኘ፣ የስልጠና ማዕከል፣ ካፍቴሪያ፣ የሠልጣኞች መኝታ ቤት፣ የኢንስቲትዩቱ የመኖሪያ ብሎኮች እና አዳራሽ የግንባታ ስራዎች ያልተጀመሩ መሆኑ፤

148. ኢንስቲትዩቱ የሚያከናውናቸው የማሽነሪ እና የላብራቶሪ መሣሪያዎች ግዥ ከህንፃ ግንባታው ፕሮግራም አፈፃፀም ጋር የተጣጣመ መሆን ሲኖርበት ኢንስቲትዩቱ አዲስ በሚያስገነባቸው ህንፃዎች ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጡ ታስበው ከውጭ ሀገር የተገዙ የላብራቶሪ መሣሪያዎችና የልብስ ስፌት ማሽኖች ሀገር ውስጥ ቢገቡም የኢንስቲትዩቱ ህንፃ ግንባታ በመጓተቱ ምክንያት መሣሪያዎችን ገጥሞ ስራ ላይ ለማዋል ባለመቻሉ መሣሪያዎቹ ከሁለት ዓመት በላይ ያለስራ መቀመጣቸውና የዋስትና ጊዜያቸው ማለፉ፤

149. ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት ላይ እየሰጠ ያለው ምክርና ድጋፍ አጥጋቢ ያለመሆኑ፤

150. ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን (ከመሠረታዊ የልብስ ስፌት ስልጠና ውጪ) በሌሎች የስልጠና ዓይነቶች ላይ ለስልጠና አገልግሎት ታስበው የተገዙት ማሽነሪዎች ተተክለው ሥራ ባለመጀመራቸው ሥልጠናው አለመሰጠቱ፤

151. ኢንስቲትዩቱ በጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች የፊዚካል የኬሚካልና ኢንቫይሮንመንታል የፍተሻ አገልግሎት በመስጠት የጥራት ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምር ማድረግ ሲጠበቅበት የሎት ሁለት ህንፃ ግንባታ ባለመጠናቀቁ ለፍተሻ አገልግሎት የተገዙትን መሳሪያዎች ተክሎ ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ አለመቻሉ፤

የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን

152. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በሰኔ 2000ዓ.ም አጠቃላይ የሀገሪቱን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ /Ethiopia Enivronment out look or the state of environment/ ቢያዘጋጅም እስከ 2004 ዓ.ም መጨረሻ ለአካባቢ ምክር ቤት በመላክ ውሳኔ እንዲሰጥበት /Endorsed/ አለማድረጉ፤

153. በ2004ዓ.ም ዘገባ ለማዘጋጀት የሚረዳ በአራት አካባቢዎች ላይ ያተኮረ (በአብጀታና ሻላ፣ አባያና ጫሞ፣ ግልገል ጊቤ 2 እና የአፋር የግጦሽ መሬትን በተመለከተ ዓመታዊ የአካባቢ ሁኔታ መግለጫ (Fact sheet) ከማዘጋጀት

ውጭ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አጠቃላይ የአከባቢ ሁኔታ ዘገባ በማዘጋጀት ለመንግስትና ለህዝብ ይፋ አለማድረጉ፤

154. የኢንዱስትሪ ብክለትን ለመከላከል በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 159/2001 ላይ በተቀመጠው መሰረት የሀገሪቱን የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚያመለክት ዘገባ እስከ 2004 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ አላማዘጋጀቱ፤ በዚህም ምክንያት በአጠቃላይ በአገር አቀፍ ደረጃ የበካይ ነገሮች መጠንና አወጋገድን የሚያመለክት መረጃ አለመኖሩ፤

155. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አደገኛ ነገሮችን /ኬሚካሎችን/ ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን በተመለከተ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲና ህግ ሊያዘጋጅ እንዲሁም የፀደቁ የአካባቢ ህጎች በስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል፣ ሊቆጣጠር እና ሊያረጋግጥ ሲገባ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲና ህግ (አዋጅ እና ደንብ) አለማዘጋጀቱ እንዲሁም የፀደቁ የአካባቢ ህጎች በስራ ላይ መዋላቸውን የማያረጋግጥ መሆኑ፤

156. በባለስልጣኑ የተዘጋጁትን የአካባቢ ደረጃዎች ስራ ላይ መዋላቸውን ለመከታተል የሚያስችል የተደራጀ የፍሳሽ መመርመሪያ ላብራቶሪ በፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሌለው መሆኑ፤

157. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ደንቦች (ለውሃ አዘል መሬቶችና ሐይቆች አጠቃቀም እና እንክብካቤ፣ ለኤሌትሮኒክ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ) እና ደረጃዎችን ደግሞ (በወንዞች፣ በሸለቆዎች እና በሐይቆች ዙሪያ ሊኖር ለሚገባው የማይደፈር ክልል (buffer zone)፣ ከተሽከካሪዎች የሚወጣው የጭስ ልቀት፣ ለሙቀት ሳቢ ጋዝ ልቀትና ለድምፅ ብክለት) አለማዘጋጀቱ፤

158. የፌዴራል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችን አያያዝ አጠቃቀምና አወጋገድ /ማምከንን/ አሰመልክቶ መመሪያ በማዘጋጀት ኢንዱስትሪዎች እንዲጠቀሙበት ባለማድረጉ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 46 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 37ቱ (80%ቱ) ኢንዱስትሪዎች በፋብሪካው ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸውና መወገድ ያለባቸውን ኬሚካሎች እንዴት ማስወገድ እዳለባቸው፣ የት መወገድ እንዳለበት ወይም እንዴት ማምከን እንደሚቻል አለማወቃቸው፤ እንደዚም ከጊዜ ብዛት ምን አይነት ጉዳት

እንደሚያደርሱ ግንዛቤ ባለመኖሩ በመጋዘን ቤቶች እና በየፋብሪካዎች ግቢ ውስጥ ብዛት ያላቸው ኬሚካሎች ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ፣

159. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጊዜ ያለፈባቸው በካይ ኬሚካሎች በሰው፣ በእንስሳት እዲሁም በእፅዋት ላይ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ክትትል እያደረገ ለሚመለከተው አካል በማሳወቅና የኬሚካል አወጋገድ መመሪያ በማዘጋጀት የሚወገዱበትን ሁኔታ አለማመቻቸቱ፣

160. የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እና ኢንዱስትሪዎች በአደገኛ ኬሚካሎች ዙሪያ ለፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የኬሚካሎቹን አወጋገድ በተመለከተ ሁኔታዎችን እንዲያመቻችላቸው ወይም የአደገኛ ኬሚካሎች ህግና መመሪያ እንዲልክላቸው በተደጋጋሚ ቢጠይቁም መፍትሄ ያልሰጣቸው መሆኑ፣

161. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ማንኛውም ነባር ፋብሪካ በ5 ዓመታት የጊዜ ገደብ ውስጥ ከፋብሪካው እንቅስቃሴ በሰዎች፣ በእፅዋትና በእንስሳት ላይ የሚከሰተው አሉታዊ ተፅእኖ ሲኖር በደንብ ቁጥር 159/2001 በተቀመጠው የ5 አመት የጊዜ ገደብ ውስጥ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲቀንስ ወይም እንዲወገድ አስተዳደራዊም ሆነ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ሲገባው አለመውሰዱ፣

162. በህዝብ አቤቱታ እና ቅሬታ መሰረት በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ እና በድሬደዋ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች አሉታዊ ተፅኖውን ለመቀነስ የሚያስችል አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ ጅማሮው ቢኖርም በተቀሩት ስምንት ክልሎች እና በነዚሁ ክልሎች ስራው ተጠናክሮ እንዲሰራ ባለስልጣኑ ጥረት አለማድረጉ፣

163. በኦዲቱ ወቅት በስድስቱ ክልሎች በናሙና ከታዩት 46 ፋብሪካዎች (የጨርቃ ጨርቅ፣ የቆዳ፣ የሲምንቶ፣ የኬሚካል፣ የስኳር፣ የምግብና የመጠጥ፣ የማተሚያ ቤት እና የብረታብረት ኢንዱስትሪዎችን የሚያጠቃልል) ውስጥ 26ቱ ፋብሪካዎች የፍሳሽ ማጣሪያ እና የአቧራና የጭስ መቆጣጠሪያ መሳሪያ የሌላቸው በመሆኑ ከፋብሪካው የሚወጣው ፈሳሽ ቆሻሻ ሳይታከም በቱቦ በመጠቀም ወደ አቃቂ፣ ሰበታ፣ ሞጆ፣ ኮምቦልቻ-ወርቃማ እና አባይ ወንዞች እና ወደ ገበሬዎች ማሳ ቀጥታ የሚለቀቅ መሆኑን እንዲሁም ፍሳሹ ጉድጓድ በመቆፈር ወደ መሬት ውስጥ እንዲሰርግ መደረጉ ከዚህም ባሻገር የፍሳሹ ውሃ በትነት መልክ ወደ አየር የሚለቀቅ መሆኑን እና ከሲሚንቶ ፋብሪካዎች የሚወጣው ጭስ እና ብናኝም ወደ አየር የሚለቀቅ መሆኑ፣

በኮሜት ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር የጭነት ትራንስፖርት፤ የመለዋወጫ ዕቃ ግዥና የንብረት አስተዳደር የአሠራር ስርዓትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት፤

164. አክሲዮን ማህበሩ ለማጓጓዝ የተስማማቸውን ጭነቶች በውሉ መሰረት ሊያከናውን እና ጊዜን መቆጠብ በሚያስችል መልኩ ዕቃዎችን መጫን፤ ማራገፍ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ሲገባ በመሰረታዊ የትራንስፖርት ቅንጅትና ትርፋማነት መመሪያ ላይ በተቀመጠው መለኪያ መሰረት በዓመት የአንድ ተሽከርካሪ በመጫን ማራገፍ ሂደት አማካይ የጊዜ ቆይታ ቀን 48.75 ቀን (17%) እንደሚፈጅ የተገለፀ ሲሆን ማህበሩ በአራቱ ዓመታት በመጫን ማራገፍ የባከነ ጊዜ እንደቅደም ተከተሉ በመቶኛ 23%፣ 34%፤ 23% እና 27% መሆኑ፤

165. ለአክሲዮን ማህበሩ የሲኖትራክ ጭነት ተሽከርካሪዎች በህዳር 30/2001 ዓ.ም የቀረበ የመለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ እስከ ጥር 19/2003 ዓ.ም በመዘግየቱ ተሽከርካሪዎቹ ለሁለት ዓመት ከሁለት ወር በላይ ያለስራ በመቆማቸው አክሲዮን ማህበሩ ተሽከርካሪዎቹ በስራ ላይ ቢሆኑ ሊያገኝ ይችል የነበረውን በአማካይ 2,688,243.48 ብር ገቢ ማጣቱ፤

166. የአክሲዮን ማህበሩ ከኢትዮ ኢንቨስትመንት የገዛቸው 15 ስካኒያ የጭነት ተሽከርካሪዎች ከተሽከርካሪው ጋር መምጣት የሚገቡ ክፍያ የተፈጸመባቸው የድጋፍ ዕቃዎችና መፍቻዎች ባለመምጣታቸው ብር 274,165.44፤ የጐን ቁጥር 79-002 ስካኒያ ተሽከርካሪ በዋስትና ጊዜ የተጠገነበት ወጪ ብር 8137.88፤ ዋጋ ተከፍሎባቸው ያልመጡ መለዋወጫዎች ብር 540,983.55 በድምሩ ብር 823,282.87 የመንግስት ገንዘብ አለግባብ መባከኑ፤

167. አክሲዮን ማህበሩ የመለዋወጫ ዕቃዎችን ግዥ ሲፈፅም የገበያ ዋጋ ዳሰሳ /market survey/በማድረግ በየስድስት ወሩ የተከለሰ የገበያ ዋጋ ዝርዝር /price list/ ማዘጋጀት ሲኖርበት የገበያ ዋጋ ዝርዝር /price list/ የማያዘጋጅ በመሆኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተከለሱ የግዥ ሰነዶች ውስጥ የመለዋወጫ ዕቃ ግዥ ሲፈፀም የገበያ ዋጋው ብር 12,244.34 ሆኖ ሳለ በግዥ ሰራተኞች የተገዛበት ዋጋ ግን ብር 27,364.59 (227%) መሆኑ፤

168. አክሲዮን ማህበሩ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የጭነት ተሽከርካሪዎችና መለዋወጫዎችን በንብረት አወጋገድ መመሪያ መሰረት ሊያስወግድ ሲገባ ብር 14,907,848.00 የሆነ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የቴክኒክ ስራ ማከናወኛ ማሽነሪዎችና መሳሪያዎች በእርጅና እና በቴክኒክ ባለሙያ ተጠንተው አክሲዮን ማህበሩ የማይጠቀምባቸው ወይም በትርፍነት የሚገኙ በመሆናቸው እንዲወገዱ አስተያየት የቀረበ ቢሆንም በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

<u>በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የተካሄደው መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት</u>

169. የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የመንግስት መስሪያ ቤቶች መሰረታዊ የአሰራር ለውጥ ተግበራዊ ካደረጉ በኋላ ያስቀመጧቸውን ግቦች ምን ያህል እንዳሳኩ ራሳቸውን እንዲገመግሙ አቅጣጫ ሊያስቀምጥና ተግባራዊነቱንም ሊከታታል ሲገባ አለመከታተሉና አለመደገፉ፤

170. የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር መሰረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ ሥርዓት ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የማበረታቻ ስርዓት ሊዘረጋ እና በሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ሊያደርግ እና የማበረታቻ ስርዓቱም ከውጤትና ከግብ ስኬት ጋር ሊያያይዝ እና የየተቋሙ ስትራቴጂ በሰራተኞች ዘንድ ትኩረት እንዲያገኝ የሚያስችል እና ስርዓቱም በተቋም፣ በቡድን እና በግለሰብ ፈጻሚዎች ደረጃ በትክክል የተዘረጋ መሆኑን ማረጋጋጥ ሲጠበቅበት ስርዓቱን አለመዘርጋቱ፤

171. በአጠቃላይ በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የታዩ ድክመቶችን በተመለከተ ኦዲት የተደረጉት መ/ቤቶች ሁሉ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ የሚያግዛቸው አስተያየቶች የተሰጡአቸው ሲሆን እነኚህን እርምጃዎች ወሰደው ያስተካከሉ ስለመሆኑ በመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና በሌሎችም ጉዳዩ በሚመለከታቸው የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች አማካይነት ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ

172. በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተር በተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተገለጹ ግኝቶች ላይ በጊዜ ገደብ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና ለመውሰድ ካልቻሉም ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ይህንኑ መነሻ የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት እንደተጠናቀቀ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ለተገኙባቸው 67 መ/ቤቶች እና 17 የክዋኔ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች የማስተካከያ መርሃ-ግብር ነድፈው እንዲያሳውቁን ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም፤ እስከአሁን መርሀ-ግብሩን የላኩት 35 (ዝርዝሩን በአባሪ 3 ይመልከቱ) መ/ቤቶች ብቻ ናቸው፡፡ እንዲዚሁም በ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ 24 መ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በአስተያየቱ መሰረት እምጃ ያልወሰዱ መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡

173. ያለበቂ ምክንያት በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በቀረቡ የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሃሣቦች ላይ በወቅቱ እርምጃ ያለመውሰድ የሕግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑ ታውቆ የእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ ም/ቤቱም በዚህ ረገድ የሚያደርገውን ክትትልና ቁጥጥር ማጠናከር ይኖርበታል፡፡

በትምህርት እና ሥልጠና ረገድ በመ/ቤቱ የተከናወኑ የአቅም ግንባታ ሥራዎች

174. የመ/ቤቱን የሰው ኃይል የመፈጸም አቅም ለማጎልበት በስትራቴጂ ዕቅዱ የተለዩትን ክፍተቶች መሠረት በማድረግ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር ጭምር የአጭርና የረጅም ጊዜ ሥልጠናዎች በመሰጠት ላይ ናቸው፡፡ በተለይ በርከታ ኦዲተሮች ለተመሠከረለት የኦዲትና የሂሳብ ባለሙያነት የሚያበቃውን የቻርተርድ አካውንታንትነት ኮርስ እንዲከታተሉና ትምህርቱንም ሲጨርሱ የተወሰኑ ዓመታት መ/ቤቱን ለማገልገል ውል እንዲገቡ የተደረገ ቢሆንም በአብዛኛው ትምህርቱን ሲጨርሱ ወዲያው ገንዘብ ከፍለው ስለሚሄዱ ሌላው

ፈታኝ ጉዳይ ነው፡፡ የሌሎች የዲግሪ ኮርሶችም ቢሆን እምቢዛም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡

የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥርዓት ግንባታን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት

175. የኦዲቱን እና ሌሎች ሥራዎችን በመረጃ ቴክኖሎጂ ለመደገፍ እና ለማጠናከር የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው የቀጠሉ ከመሆኑም በላይ የመ/ቤቱ የNet work Infrastructure እና ደህረ-ገፅ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል የውስጥ ግንኙነቱን የመረጃ ፈሰትና ልውውጥ እንዲያቀላጥፍ የExchange server ገጠማና ፍተሻ ሥራዎች እንደዚሁም የ wireless net work configuration ተግባራት ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ የሂሣብ እና የኦዲት ሶፍትዌሮች ላይ ለሠራተኛው ተገቢው ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

የኮሙኒኬሽን ሥራን በተመለከተ የተሠሩ ሥራዎች

176. የመ/ቤቱ ተልዕኮ በማሳካት ረገድ ጉልህ ሚና ያላቸው ባለድርሻ አካላትን በተመለከተ መ/ቤቱ ስለሚሠራቸው ሥራዎች በቂ የሆነ ግንዛቤ ኖሯቸው አስፈላጊውን ድጋፍ እና እገዛ ለማድረግ እንዲችሉ በየጊዜው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎች እና ወርክሾፖች በማካሄድ ላይ እንገኛለን፡፡ በዚህም መሠረት ለምክር ቤት አባላትና ለፍትህ እና ህግ አስፈፃሚ አካላት እንደዚሁም ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ

177. በዚህ ረገድ በመ/ቤታችን ጠንካራ ሥራ ተሰርቷል ብሎ መናገር ባይቻልም በሥርዓታ ፆታ፣ በ HIV/AIDS እና በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ ከመ/ቤቱ አስፈላጊው ድጋፍ እየተሰጠ ሥራዎቹን በሚያስተባብሩ ኮሚቴዎች አማካይነት ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንና የHIV/AIDS ቀን በመ/ቤት ደረጃ በማክበርና ዓመታዊ የችግኝ ተከላ ተግባራት ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም የመ/ቤታችን ሴት ሰራተኞች በየሁለት ወሩ ግማሽ ቀን የጋራ የምክክርና የልምድ መለዋወጫ መድረክ እንዲኖራቸው ተወስኗል፡፡ ነገር ግን ስራዎቹን በቋሚነት መደበኛ ሠራተኛ ተመድቦላቸው እንዲከናወኑ ለማድረግ በርካታ ጥረት ቢደረግም

ባለመሳካቱ አሁንም መ/ቤቱ የተለያዩ አማራጮችን በመመልከት ላይ ይገኛል፡፡

ለኦዲተሮችና የሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ማረጋገጫ መስጠትና ማከታተልን በተመለከተ

178. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5/16 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከጥር 2004 እስከ ታህሣሥ 2005 ባለው ጊዜ ለ8 የግል ኦዲተሮችና 107 የግል ሂሣብ አዋቂዎች አዲስ የሙያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሰጥቷል፡፡

179. ቀደም ሲል ፈቃድ በተሰጣቸውም ላይ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የ494 የሂሳብ አዋቂዎችና የ64 ኦዲተሮች ዓመታዊ የሙያ የሰርትፍኬት ዕድሳት የተከናውነ ከመሆኑም በላይ የስም ዝርዝራቸውም በመ/ቤቱ ዌብ ሣይትና በጋዜጣ እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን ከዚህ ውጪ አገልግሎት እንሰጣለን የሚሉት ሲያጋጥሙ ሕገ ወጥ በመሆናቸው ለእርምጃ አወሳሰድ እንዲያመች ኀብረተሰቡ ለመ/ቤታችን ጥቆማ የሚቀርብበትን ሥርዓት እንዲያውቀው ተደርጓል፡፡

የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ

180. ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል ለኦዲት ባለሙያ 393 እና ለድጋፍ ሰጪ 252 በድምሩ 645 ሲሆን በጥር ወር 2004 የኦዲት ሥራው ሲጀመር የነበረው የሰው ሀይል 236 ኦዲተሮችና 138 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 374 ነበር፡፡ በኦዲት ዓመቱ 34 ኦዲተሮችና 19 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በድምሩ 53 ሠራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን 3 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ 1 በሞት የተለየ፣ 29 ኦዲተሮችና 9 ድጋፍ ሰጪ በድምሩ 38 ሠራተኞች በራሣቸው ፈቃድ መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

181. በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ የኦዲት ባለሙያዎች 161 ወንዶችና 81 ሴቶች በድምሩ 243፤ የድጋፍ ሰጪ 75 ወንዶችና 67 ሴቶች በድምሩ 142 ሠራተኞች በአጠቃላይ 385 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን 260 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

የ2004 በጀት ዓመትና 2005 በጀት ዓመት

የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም

182. በ2004 በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ ብር 17,529,180.52 በጀት ተፈቅዶ ብር 16,168,818.57 ወይም 92.23% ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን ለ2005 በጀት ዓመት ዕቅድ ማስፈጸሚያ ለመ/ቤታችን ከተፈቀደው ብር 18,687,730.00 ውስጥ ደግሞ እስከ መጋቢት 2005 መጨረሻ ድረስ ብር 12,787,304.02 ወይም 68.43%. ሥራ ላይ ውሏል፡፡

183. በተጨማሪም የመ/ቤታችን የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ በምክር ቤቱ በተሰየሙ ከክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በተውጣጡ የኦዲት ቡድን አባላት ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ቀርቧል፡፡

መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች

184. መ/ቤታችን በሕገ-መንግሥትና የማቋቋሚያ አዋጁ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ቢሆንም፣ በተጋረጡበት አንዳንድ ተግዳሮቶች ምክንያት ያሰበውን ያህል ውጤት ማስገኘት አልቻለም፡፡ በሥራ ላይ እየተፈታተኑን ከሚገኙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

185. ባለፉት ዓመታት የኦዲት ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ ያደገ በሆንም ኦዲቱን በሚፈለገው ጥልቀትና ጥራት ለማከናወን የሚያስችል በቂ ክህሎትና ልምድ ያለው ባለሙያ ለመቅጠር ባለመቻሉና ከፍተኛ ልምድ ያለቸው ነባርም ሆኑ አዲስ ተቀጣሪ ሠራተኞች ከደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ማነስ ጋር በተያያዘ መ/ቤቱን በመልቀቃቸው እስከ አሁን በተገኙ ውጤቶች ቀጣይነትና ሊሠሩ በታቀዱት ሥራዎች ላይ ከፍተኛ ሥጋት ፈጥሯል፡፡ የችግሩን አሳሳቢነት በማሳየትና በማስረዳት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት ቢደረግም እስከ አሁን ድረስ መፍትሔ ሊገኝ አልቻለም፡፡

186. በኦዲት ተደራጊዎች ለኦዲቱ ሥራ የሚደረገው ትብብር በአብዛኛው መሻሻል ያሳየ ቢሆንም ቁጥሩ በማይናቅ መ/ቤቶች አሁንም ያለመተባበር (በወቅቱ የሥራ ቦታ አለማመቻቸትና መረጃ አለመስጠት) ችግሮች የሚታዩ በመሆኑ

መ/ቤቶቹ በፍጥነት እነኚህን ችግሮች በማስወገድ ሕጋዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

187. ከለፈው የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ በተለየ ሁኔታ 70 (59.8%) የሚሆኑት (ዝርዘሩን በአባሪ ሁለት ይመልከቱ) የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ዘግይተው በመዝጋታቸው የዘመኑን የኦዲት ሥራ በወቅቱ እንዳናጠናቅቅና የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በመርሀ-ግብራችን መሠረት እንዳንጀምር ከፍተኛ እንቅፋት ሆኖ አልፏል፡፡ ኦዲቱን ከማቋረጥ ይልቅ የየመ/ቤቶቹን የበላይ ኋላፊዎች በተደጋጋሚ በማነጋገር ችግሩን በማስታመም የዘመኑን ኦዲት የማጠናቀቅ ኋላፊነታችንን የተወጠን ቢሆንም ጉዳዩ የሕግ ጥሰት በመሆኑ ለወደፊቱ እንዳይደገም መ/ቤቶች ከወዲሁ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ ሂሳባቸውን የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ ባስቀመጠው የሕግ የጊዜ ገደብ ውስጥ ዘግተው ለኦዲት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

188. በአብዛኛው መ/ቤቶች የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍሎች አሁንም በማዋቅር፣ በክህሎትና በዕውቀት በሚገባ ባለመደረጀታቸውና አንፃራዊ ነፃነታቸው ተጠብቆ እንዲሠሩ ባለመደረጉ ወይም ባለመፈቀዱ የውጪ ኦዲቱ ከውስጥ ኦዲት ሥራ ማግኘት የሚገባውን ባለማግኘቱ ሰፊ ሥራ እንዲሠራ መገደዱ፣

189. ሌላው አሁንም ያልተሻገርነው ችግር በርካታ ኦዲት ተደራጊዎች ከመ/ቤታችን በሚላኩ የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠትና በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረት በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ ነው፡፡ አሁንም ቢሆን ተገቢውን እርምጃ የማይወስዱ ኦዲት ተደራጊዎች ይህ ጉዳይ ውሎ አድሮ ተጠያቂነትን ሣያስከትል አስቀድው ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ቢወስዱ ተመራጭ ይመስለናል፡፡ በም/ቤቱም በኩል የማስተካከያ እርምጃ በማይወስዱ ኦዲት ተደራጊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

<u>የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ዕቅድ</u>

190. ባለፉት የበጀት ዓመታት ኦዲት ወቅት እንዳደረግነው ሁሉ የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲትንም ስናቅድ አንዱ ተኩረታችን የኦዲት ሽፋንን ከፍ

መድረግ ነው፡፡ በዚሁም መሠረት የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ሽፋኑን 100%፣ የክዋኔ ኦዲትን ደግሞ 28፣ የመሠረታዊ አገልግሎት ክለላ ተከታታይ ኦዲትን ደግሞ በቁጥር 298 ለማድረስ ታቅዷል፡፡

191. በዚሁ መሠረት ከጥር እስከ መጋቢት 30/2005 ባሉት ሶስት ወራት ጊዜ 80 የፋይናንስና ሕጋዊነት፣ 17 የክዋኔ እና 72 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ክለላ ተከታታይ ኦዲቶች ተጀምረው በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ከመሆኑም በላይ በአጠቃላይ የኦዲቱ ሥራ በታቀደው መሠረት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወነ ኦዲት

192. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ኃላፊነት ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሳቦችን በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽኑ እና ከመ/ቤቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት አስደርጎ በሚቀርቡ ሪፖርቶች መነሻነት አስፈላጊው የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደረጊ ድርጅቶች፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በደብዳቤ አስፈላጊው ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

193. በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በ2004 በተከናወኑ ኦዲቶች የታዩ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ ጥራዝ 2 ክፍል 3 በዝርዝር የቀረበ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ኦዲት የተደረጉ ድርጅቶች የሂሣብ መግለጫ ሁኔታ

194. በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 82 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በውጭ መንግሥታት የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሣብ ደግሞ 150 በድምሩ 232 (ይህ ቁጥር በአንድ በጀት ዓመት የአንድ መ/ቤት የሁለት እና

ከዚያ በላይ ሂሳብ ኦዲት የተደረገ ከሆነ የቅርቡን በጀት ዓመት ብቻ እንደ አንድ በመቁጠር የተወሰደ ነው) ኦዲቶች ተከናውኗል፡፡

195. በእነዚህ ሪፖርቶች ላይ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ዓይነት ሲተነተን፤ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Unqualified opinion) 87፣ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት (Qualified opinion) 142፣ አቋም የማይወሰድበት አስተያየት (Disclaimer opinion) 2 እና ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት (Adverse opinion) የቀረበበት 1 በድምሩ 232 ናቸው፡፡

196. በሌላም በኩል እስከ ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓ.ም. መጨረሻ ባለው መረጃ መሠረት ከሁለት ዓመታት በላይ ሂሣባቸውን ዘግተው ኦዲት ያላስደረጉ 20 የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና መ/ቤቶች ይገኛሉ፡፡

197. የኦዲት አንዱ ጠቀሜታ ወቅታዊ የሆነ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ስለሆነ ከረጅም ጊዜ በኋላ ኦዲት ተደርጎ የሚቀርበው ሪፖርት እርምጃ ለመውሰድ አስቸጋሪ በመሆኑ፤ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት እነዚህ ድርጅቶች ሂሣባቸውን ዘግተው ኦዲት እንዲያስደርጉ በቅርበት ሊከታተሉት ይገባል፡፡

<u>የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን</u>
<u>የሥራ እንቅስቃሴና ያጋጠሙ ችግሮች</u>

198. የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን በአዋጅ ቁጥር 126/1969 የተቋቋመ ሲሆን፣ ዓላማው፤ የመንግስት ወይም አብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት ለተያዙ የማምረቻ፣ የማከፋፈያና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት ማበርከት ነው፡፡

<u>የኮርፖሬሽኑ የዕቅድ ክንውን</u>

199. በ2004 በጀት ዓመት መጀመሪያ በነበረው 116 የሰው ኃይል 240 ኦዲቶችን ለማድረግ አቅዶ 234 ኦዲቶችን ወይም የዕቅዱ 97.50% ለመፈጸም ችሏል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የሰው ኃይል በመሳሳቱ፤ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በነበረው የሰው ኃይል ዕቅዱ በመነደፉ ነው፡፡

የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ

200. ኮርፖሬሽኑ በ2004 በጀት ዓመት ከኦዲት ሥራ አገልግሎት ብር 12.83 ሚሊዮን ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር 13.99 ሚሊዮን ገቢ አግኝቷል፡፡ በሌላም በኩል ብር 8.69 ሚሊዮን ወጪ ለማድረግ አቅዶ ብር 9.84 ሚሊዮን ወጪ ያደረገ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ የብር 4.15 ሚሊዮን ትርፍ ሊያገኝ ችሏል፡፡

ኮርፖሬሽኑ ባካሄዳቸው ኦዲቶች የታዩ አጠቃላይ ችግሮች

201. ኮርፖሬሽኑ በመንግስት ልማት ድርጅቶች ባካሄዳቸው ኦዲቶች የታዩ አጠቃላይ ችግሮች በርካታ ሲሆኑ በተለየ ጥራዝ በቀረበው ዘገባ በዝርዝር የተጠቀሱ ቢሆንም ዋና ዋናዎቹ፤

- በርካታ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ ዝርዝር መዝገብ የሌላቸው፣ ያላቸውም ቢኖሩ በአብዛኛው መዝገባቸው ያልተሟላ፣ አንዳንዶች ደግሞ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶችን በአንድ ላይ መዝግበው የተገኙ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች በመጋዘን የሚገኙ ዕቃዎችን ቆጠራ የማያደርጉ ወይም በከፊል ቆጠራ የሚያደርጉ ሲሆን፤ ሌሎቹ ደግሞ ቆጠራ ቢያደርጉም ከሂሣብ መዝገብ ጋር የማይገናዘብ መሆኑ፣
- አብዛኞቹ ድርጅቶች በርካታ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ሂሣብ የተገኘባቸው ሲሆን ሂሣቡን ለመሰብሰብ ተገቢውን ጥረት ያላደረጉ ከመሆኑም በላይ አጠራጣሪ ለሆኑት ተሰብሳቢ ሂሣቦች በቂ መጠባበቂያ ያልያዙ መሆኑ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች የሚሰበሰብ ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ የማይደረግ ከመሆኑም በላይ አልፎ አልፎ ከተሰበሰበው ገንዘብ ላይ ክፍያ የሚፈጽሙ መሆኑ፣
- በርከት ያሉ ድርጅቶች ለመንግሥት መክፈል የሚገባቸውን ከደመወዝ የተቀነሰ የሥራ ግብር፣ የጡረታ መዋጮ እንዲሁም የንግድ ትርፍ በወቅቱ የማይከፍሉ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ሂሣባቸውን በወቅቱ አለመዝጋታቸውና እንዲዘጉም የሚደረገው ግፊት የሚፈለገውን ያህል አለመሆኑ፣

➢ አንዳንድ ድርጅቶች ተከፋይ ብለው ከያዙት ሂሣብ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ሣይከፈሉ የቆዩና ለማን መከፈል እንዳለባቸው የማይታወቁ ሂሣቦች መኖሩ፣

ናቸው፡፡

ማጠቃለያ

202. በሪፖርቱ እንደተመለከተው በ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው ኦዲት በሂሳብ ምርመራ ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የተያዙትን ጨምሮ የኦዲት ሽፋኑን 96.12% ደርሷል፡፡ የኦዲት ዕቅድ ክንውናችንም የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት 100% እና የክዋኔ ኦዲቱም 19 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዶ 17ቱ (89.5%) ሲጠናቀቁ ሌሎች በዳሰሳና ቅኝት ደረጃ የሚገኙ 10 ክዋኔ ኦዲቶች ወደ ቀጣዩ ዓመት የተላለፉ ስለሆነ፤ በተለይ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን በተመለከተ ውዝፍ የኦዲት ሥራ ባለመኖሩ ወቅታዊ የኦዲት መረጃን ማመንጨት ተችሏል፡፡ ይህ ውጤት ከፍተኛ የባለሙያ ፍሰት ባለበት ሁኔታ ውስጥ በመገኘቱ ግን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

203. ውዝፍ የኦዲት ሥራ አለመኖሩና ሁሉንም የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶችን በየዓመቱ ኦዲት እናድርግ የምንልበት ደረጃ ላይ መገኘታችን የሀገራችንን የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት የተሻለ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያመለክት ቢሆንም፤ አሁንም በየመ/ቤቱ በተደጋጋሚ የሚታዩ ተመሳሳይ ነገር ግን ትኩረት ቢሰጣቸው ኖሮ ሊወገዱ የሚችሉ ግድፈቶች በአፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡ ዝርዝር ሪፖርቱ በሁለት ጥራዝ ተዘጋጅቶ፤ የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርት ደግሞ በ17 ጥራዝ ለአፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት የተላከ በመሆኑ፤ በም/ቤቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩል በጥልቀት መርምሮ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

204. በሌላ በኩል አሁንም እርምጃ ሳይወሰድባቸው ከዓመት ወደ ዓመት የሚተላለፉ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣቦች፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚፈጸሙ ግዥዎች፣ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ በየዓመቱ የሚታዩ ተደጋጋሚ ችግሮችና ከውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ አጠቃቀምና ሪፖርት አደራረግ አንፃር የሚታዩ ችግሮች፤ እንደዚሁም በመንግሥት ንብረት አያያዝና

አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች ልዩ ትኩረት አግኝተው በጊዜ የተገደበ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸው ሊስተካከሉ ይገባል፡፡

205. በተጨማሪም በሚቀርቡት የኦዲት ሪፖርቶች ላይ በሚሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶች መሠረት እርምጃ የማይወስዱ አካላትን በተመለከተ ም/ቤቱ ተገቢ ነው የሚለውን እርምጃ በመውሰድ ችግሩን ለማቃለል ጥረቱን ይበልጥ ሊያጠናክር ይገባል፡፡

206. በመጨረሻም እስከ አሁን የተገኘውን ውጤት ጭምር ወደ ኋላ ለመመለስና የወደፊቱን አፈፃፀም ሊጎዳ በሚችል መጠን መ/ቤቱን በሁሉም ደረጃ እየተፈታተና የሚገኘውን የሠራተኛ ፍሰት ችግር ለማቃለል ም/ቤቱ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ እየጠየቅሁ በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

አባሪ 1

ተ.ቁ.	የልማት ድርጅቱ ሥም	ተከራይ (አጋር) ባለሃብት	ያልከፈለው የዕዳ መጠን	የዕዳው ዓይነት
1	አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ	አቲላ ይልድሪም	ብር 25,579,395.55	የኪራይ ክፍያ እና ሌሎች እዳዎች
2	አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ	ናሪን ኦርሚ ቴክስታይል	760,000 ሺ.ህ የአሜሪካን ዶላር	የኪራይ ክፍያ
3	አዋሳ ጨርቃ ጨርቅ	ናሪን ኦርሚ ቴክስታይል	ብር 72 ሚሊዮን	የኪራይ ክፍያ እና ሌሎች እዳዎች
4	ሲሊ እርሻ ልማት	ሬድ ስፔክልድ ኢትዮጵያ	ብር 1,685,090.22	የኪራይ ክፍያ እና ሌሎች እዳዎች
5	ሲሊ እርሻ ልማት	ሉሲ እርሻ ልማት	ብር 1.711 ሚሊዮን	የኪራይ ክፍያ
6	አምቦ ውሃ አክሲዮን ማህበር	ሳብ ሚለር	ብር 4,499,309	የድርጅቱ እዳ
7	አደሌ እርሻ ልማት	አፊያ የምግብ ኮምፕሌክስ	ብር 1,006,416.8	የኪራይ ክፍያ
	በድምሩ		ብር 106,481,211.57	
			760,000 የአሜሪካን ዶላር	

ሂሳባቸውን በወቅቱ ያልዘጉና ዘግይተው ለኦዲት ያቀረቡ መ/ቤቶች

ተ. ቁ.		የመ/ቤቱ ስም	የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
		የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	
1	1	የግብርና ሚኒስቴር	18/04/05
2	2	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	15/03/05
3	3	የውና ኢነርጂ ሚኒስቴር	29/02/05
4	4	የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	20/04/05
5	5	የኢትዮጵያ መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን	7/3/2005
6	6	የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	2/4/2005
7	7	የማዕድን ሚኒስቴር	12/3/2005
8	8	የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት	21/02/05
9	9	የኢ.ት. ሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዮት	26/02/05
10	10	የብሄራዊ ነዳጅ መጠባበቂያ ዴፖዎች አስተዳደር	12/3/2005
11	11	የኢትዮጵያ ጤናና ሥነ ምግብ ኢኒስቲትዩት	5/3/2005
12	12	ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	23/02/05
13	13	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	11/3/2005
14	14	የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ	19/02/05
15	15	የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን	13/02/05
16	16	የህብረት ሥራ ኤጀንሲ	19/03/05
17	17	የሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	5/3/2005
		የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	
18	1	የፌደራል ፖሊስ	3/4/2005
19	2	ንግድ ሚኒስቴር	3/3/2005
20	3	ፍትህ ሚኒስቴር	3/3/2005
21	4	የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት	3/3/2005
22	5	የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም	3/4/2005
23	6	ሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ	3/3/2005
24	7	የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን	3/3/2005
25	8	የኢትዮጵያ አክሬዴቴሽን ጽ/ቤት	3/4/2005
26	9	የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት	1/4/2005
27	10	የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት	11/3/2005
28	11	የፌደራል ሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን	19/02/2005
29	12	የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	6/2/2005

ተ. ቁ.		የመ/ቤቱ ስም	የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
30	13	የቆዳኢንዱስትሪልማት ኢንስቲትዩት	5/2/2005
31	14	የኢ.ት. ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ	17/03/05
32	15	የኢ.ት. ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	26/02/05
33	16	የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ	26/03/05
34	17	ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት (የተጠቃለለ)	26/3/2005
35	18	ፌደራል ጉዳዮች ሚ/ር	30/2/2005
36	19	ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	22/2/2005
37	20	ብረታ ብረት ልማት	6/3/2005
38	21	የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	26/03/2005
39	22	የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች ሥልጠና ማዕከል	3/3/2005
40	23	ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	14/03/2005
41	24	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	26/03/2005
		የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	
42	1	ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር	30/02/05
43	2	ትምህርት ሚኒስቴር	5/4/2005
44	3	ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ	30/02/05
45	4	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	9/4/2005
46	5	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	18/03/05
47	6	ወሎ ዩኒቨርስቲ	10/3/2005
48	7	ሠመራ ዩኒቨርስቲ	27/03/05
49	8	ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ	17/03/05
50	9	አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	28/02/05
51	10	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	9/2/2005
52	11	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	14/03/05
		የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	
53	1	የኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ	21/05/2005
54	2	የማዕከላዊ እስታስቲክስ ኤጀንሲ	21/02/2005
55	3	የሴቶችና የወጣቶችና የህፃናት ጉዳዮች	21/02/2005
56	4	የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት	9/2/2005
57	5	የወለጋ ዩኒቨርስቲ	22/02/2005
58	6	የኢ.ት. ፕሬስ ድርጅት	26/02/2005
59	7	የቤተመንግስት አስተዳደር ጽ/ቤት	21/02/2005
60	8	የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	4/3/2005
61	9	የድሬደዋ ዩኒቨርስቲ	21/02/2005
62	10	የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ	14/03/2005
63	11	የፕሬዘዳንት ጽ/ቤት	5/4/2005

ተ. ቁ.		የመ/ቤቱ ስም	የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
64	12	ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጽሐፍት ኤጀንሲ	22/02/2005
65	13	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ስብሰባ ማዕከል	9/2/2005
66	14	የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት	13/02/2005
67	15	የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	22/02/2005
68	16	የኢት. ብሮድካስት ባለስልጣን	26/03/2005
69	17	የመንግስት የፋይናንስ ድርጅት ኤጀንሲ	6/2/2005
70	18	የመንግሥት አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ/2003/	10/8/2004

ለ2004/2005 ኦዲት የድርጊት መርሀ ግብር የላኩ መ/ቤቶች ዝርዝር

ተ.ቁ.	የመ/ቤቱ ስም	ምርመራ
1	የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ	ክዋኔ ኦዲት
2	በኘራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የመንግስት የትርፍ ድርሻና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር አሰጣጥ አጠቃቀም እና አሰባሰብ	“ “
3	በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የአካባቢ እንክብካቤ ሥርዓት አተገባበር	“ “
4	ኘራይቤታይዜሽን በጋራና በኪራይ የሚተዳደሩ	“ “
5	በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታ ፈንድ አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም ክዋኔ ኦዲት	“ “
6	ማዕድን ሀብት ልማትና አካባቢ ተፅዕኖ	“ “
7	ኢምግሬሽንና ስደተኞች መደበኛ ፖስፖርት አሰጣጥ	“ “
8	የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የፌዴራል መንግሥት ቢሮዎች ህንፃ ግንባታ	“ “
9	ከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ	የፋይናንሻል ኦዲት
10	የአክሱም ዩኒቨርስቲ	“ “
11	ጐንደር ዩኒቨርስቲ	“ “

ተ.ቁ.	የመ/ቤቱ ስም	ምርመራ
12	መደወላቡ ዩኒቨርስቲ	“ “
12	ወላይታሶዶ ዩኒቨርስቲ	“ “
13	ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ	“ “
14	መቀሌ ዩኒቨርስቲ	“ “
15	ባህርዳር ዩኒቨርስቲ	“ “
16	አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ	“ “
17	አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ሚኒስቴር	“ “
18	ሰመራ ዩኒቨርስቲ	“ “
29	የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	“ “
20	የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	“ “
21	የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	“ “
22	የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ	“ “
23	የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ኤጀንሲ	“ “
24	የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	“ “
25	የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ	“ “
26	የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	“ “
27	ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር	“ “
28	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	“ “
29	የኢትዮጵያ ካርታ ስራ ኤጀንሲ	“ “
30	የኢትዮጵያ ጨረር መከላከያ ባለስልጣን	“ “

ተ.ቁ.	የመ/ቤቱ ስም	ምርመራ
31	የኢትዮጵያ ኘሬስ ድርጅት	“ “
32	ወለጋ ዩኒቨርስቲ	“ “
33	ደብረ ብርሀን ዩኒቨርስቲ	“ “
34	ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	“ “
35	ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጽሐፍት ኤጀንሲ	“ “
36	ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር	“ “
37	ግብርና ሚኒስቴር	“ “
38	የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	“ “
39	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	“ “
40	የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን	“ “
41	የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	“ “